ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ | 83 ዓመት ቁጥር 265 ግንቦት 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



## “ሀገራዊ ምክክር ሁሉንም አሸናፊ ያደርጋል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክር ሁሉንም ወገን አሸናፊ የሚያደርግ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ጦርነትና አብዮት የተሟላ መፍትሔ የማያመጡት አሸናፊ እና ተሸናፊ ስለሚያስከትሉ ነው። ቢዘገይም የተሸነፈው ለማሸነፍ ይታገላል። ያሸነፈውም ድሉን ለመጠበቅ ይዋጋል። ምክክር ግን ሁሉንም አሸናፊ ያደርጋል። ከተሸነፍንም ሁላችንም ለሀገራችን ብለን ነው የምንሸነፈው ነው ያሉት።

ጦርነትን ኖረንበታል። የተወሰኑ ችግሮቻችንን ፈትተንበታል። አብዮትን ደጋግመነዋል። የተወሰኑ ችግሮችን ፈትተንበታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ በሁለቱም ያልተፈቱትን ችግሮች ለመፍታት የቀረን መንገድ ምክክር ነው። ምክክርን ግን አልተጠቀምንበትም ብለዋል።

የምክክር ሂደቱ ሦስት ነገሮች እንደሚያስገኝ ገልጸው፤ እነዚህም ሁሉንም ባይሆን እንኳን ዋና ዋና ችግሮችን እንደሚፈታ፤ ከጦርነት ይልቅ ምክክር ባህል እንዲሆን እንደሚያደርግ፤በተቃራኒ ኃይሎች መካከል መቀራረብና መግባባት እንደሚፈጥር ጠቅሰዋል።

ይሄንን መቀራረብ በመጠቀምም ወደፊት በጉዳዮች እየተነጋገርን ለመቀጠል ያስችለናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤በመሆኑም ይህንን እድል ሳናበላሽ ወደ ተሟላ ድል እንድናሽጋግረው እጠይቃለሁ ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

## ኮሚሽኑ ፈተና ቢገጥመውም ሳይበገር መግባባትን ለማምጣት እየሠራ ነው

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ከተማ አቀፍ ምክክር ተጀመረ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ፈተናዎች ቢገጥሙትም ፈተናዎቹ ሳይበግሩት ብዙዎች ሲመኙት የነበረውን መቀራረብንና መግባባትን ለማምጣት ሥራውን እያከናወነ መሆኑን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ገለጸ፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን የምክክር ምዕራፍ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት አስጀምሯል።

በዓድዋ ድል መታሰቢያ ትናንት በተጀመረው ከተማ አቀፍ የምክክር ምዕራፍ የኅብረተሰብ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሦስቱ የመንግሥት አካላት ማለትም ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ፣ የተቋማትና የማህበራት ተወካዮች፣ የተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡

በምክክር ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ላይ ንግግር ያደረጉት የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ር)

ኮሚሽኑ ፈተና...ወደ ገጽ 4 ዞሯል













## ፈተናውን በብይነመረብ ለመስጠት መታቀዱ ኩረጃን ለማስቀረት ዘላቂ መፍትሔ ነው

-የ12ኛ አገር አቀፍ ፈተናን ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው

ገጽ 4



ዜና



አቶ ያሬድ ኃይለ ማርያም

# በሽግግር ፍትሕና

## በሀገራዊ ምክክሩ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች በጥልቀት ሊታዩ ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሽግግር ፍትሕና በሀገራዊ ምክክሩ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች በጥልቀት ሊዳሰሱ ይገባል ሲሉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ገለጹ። ለሽግግር ፍትሕና ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋችና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል ዋና ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ኃይለ ማርያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሽግግር ፍትሕና በሀገራዊ ምክክሩ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች በጥልቀት ሊዳሰሱ ይገባል።ይህን ማድረግ ሲቻልም ሰብዓዊ መብቶች በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻልባቸውን ሁኔታ ይፈጥራል።

አቶ ያሬድ ለሽግግር ፍትሕ የወጣው ፖሊሲ በትክክል ተተርጉሞና ተግባራዊ ተደርጎ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ውስብስብ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለመቅረፍ ያለው እድል በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸው፤በቀጣዩ ሂደትም በግጭትና በተለያዩ ጉዳዮች ሰብዓዊ መብት የተጣሰባቸው ሰዎችን አካታች መሆን አለበት ብለዋል።

የሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትሕ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ከማስቀረት ረገድ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ያሬድ፤በቀውስ ውስጥ ለቆየና ብዙ የሰብአዊ መብት ለተጣሰባቸው ዜጎች ፍትሕን የሚያሰፍን መሆኑን ጠቁመዋል።

በምክክሩና በሽግግር ፍትሕ ሙሉ በሙሉ በገለልተኛ አካል ከተካሄደ እንዲሁም ሁሉም በንቃት መሳተፍ ከቻለ የሰብዓዊ መብት ችግር ከመፍታት በተጨማሪ በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ልዩነቶችና ቀውሶች በዘላቂነት መፍታት የሚችሉ መሆናቸውንም ነው አቶ ያሬድ ያብራሩት።

የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ከጅምሩ ጀምሮ ያሉ ክፍተቶች ላይ በመወያየት የነቃ ተሳትፎ ሲያደርጉ ነበር ያሉት አቶ ያሬድ፤ በሂደቱ ከመሳተፍ ጎን ለጎን ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ አቶ ያሬድ ገለጻ፤ ለውጤታማነታቸውም መንግሥትም ሆነ ነፍጥ ያነገቡ አካላት ቀድመው ለሰላምና ለእርቅ በመዘጋጀት መነጋገርና መወያየት ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም ለሰላም የሚከፈል የትኛውም አይነት ዋጋ ተከፍሎ ቅድሚያ ሰላም ማስፈን አስፈላጊ ነው።

የሽግግር ፍትሕና የሀገራዊ ምክክሩ ግጭት በሚታይባቸው አካባቢዎች ያሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መፍትሔ ለመስጠት ያሉ ብቸኛ አማራጭ ናቸው ብለዋል።

አሳታፊነት፣ ገለልተኝነት እንዲሁም ተዓማኒነት በመገንባት ሀገራዊ ምክክሩና የሽግግር ፍትሕ የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያስገኝና ሰብዓዊ መብት እንዲያሰፍን ትኩረት መደረግ አለበት ያሉት ደግሞ ሌላኛው የሰብአዊ መብት ተሟጋች አቶ ጌቱ ሳቀታ ናቸው።

የሚቀሩ ሥራዎች ቢኖሩም እስካሁን የተኬደበት ርቀት የሚበረታታና የሚደገፍ ነው ያሉት አቶ ጌቱ፤ ሀገራዊ ምክክሩና የሽግግር ፍትሕ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ማስቀረት የሚችሉና በታሪክ አጋጣሚ አንዴ የተገኙ መልካም እድሎች በመሆናቸው ሁሉም ዜጋ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ይገባዋል ብለዋል።

የሀገር ሽማግሌዎች፣የሃይማኖት አባቶች፣መንግሥት፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችና ዜጎች የሀገሪቱ ሰላም እንዲረጋገጥ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ መወጣት እንደሚጠበቅባቸውም መክረዋል።

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስፈን ከሀገራዊ ምክክሩና ከሽግግር ፍትሕ በተጨማሪ በሀገሪቱ የሚገኙ መልካም ባህሎችና እሴቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው።

# በአማራ ክልል ዘንድሮው ከአንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በዘንድሮው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከአንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን በላይ ችግኞች እንደሚተከሉ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ እስመለዓለም ምህረቱ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ ነው። በዚህም በክልሉ ሁሉም ዞኖች ለቀጣዩ አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞችን አፍልቶ ለመትከል እቅድ ተይዟል።

በአማራ ክልል በዘንድሮው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከአንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ ያሉት አቶ እስመለዓለም፤ እስካሁን በተከናወነ ሥራም ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለቆጠራ መድረሳቸውን ተናግረዋል።

እየተዘጋጁ ከሚገኙት ችግኞች መካከል ፍራፍሬዎችን ጨምሮ ዋንዛ፣ ወይራ፣ የሐበሻ ጽድ እና ሌሎች እንደሚገኙበት ጠቅሰው፤ ከችግኝ ዝግጅቱ ጎን ለጎን የመትከያ ቦታ የመለየት ሥራ በማከናወን እስካሁን ከ201 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የተከላ ቦታ መለየቱን ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ ምን አይነት ችግኝ በየትኛው ቦታ ይተከላል እና መሰል ጉዳዮች ተለይተዋል። ለመትከያ አገልግሎት ለሚውሉ ቦታዎች የካርታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የማዘጋጀት ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ በተከላ ቦታዎቹ የሳተላይት ቁጥጥር እንደሚከናወን ገልጸዋል።

እስከ አሁን ከ30 ሺህ ሄክታር በላይ ለሚሆነው መሬት ካርታ ተዘጋጅቷል። የክልሉ የአረንጓዴ አሻራ የዝግጅት ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ገልጸው፤ የአምና ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን የሚያመላክት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለዞኖች ተልኳል። በዚህም የአረንጓዴ አሻራን የሚያስተባብር ኮሚቴ በየመስሪያ ቤቱ ተቋቁሟል ብለዋል።

የአማራ ክልል አረንጓዴ አሻራ በ2015 ዓ.ም የተተከለ ችግኝ አንድ ነጥብ 52 ቢሊዮን ነው። በዚሁ ዓመት በክልሉ የተደረሰበት የደን ሽፋን 15 ነጥብ 74 በመቶ ነው ያሉት አቶ እስመለዓለም፤ በክልሉ የተተከሉ ችግኞች የጽድቀት መጠን 79 ነጥብ ስድስት በመቶ መሆኑን ተናግረዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በዘንድሮ ዓመት አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል። የችግኝ ቁጥር በሄክታር ሲሰላ ዘንድሮ ተከላ የሚደረግበት አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንደሚሆን ግብርና ሚኒስቴር ገልጿል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት በተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ከ32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸው ተመላክቷል።

በቀጣይ ሦስት ዓመታት ደግሞ 17 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በመትከል 50 ቢሊዮን ችግኞችን በስምንት ዓመታት ውስጥ ለመትከል እቅድ ተይዟል። እስካሁን ለተተከሉት ችግኞች በተደረገው ክትትል እና እንክብካቤ የችግኞቹ የጽድቀት መጠን ከ90 በመቶ በላይ መድረሱም ተገልጿል።

# በጥሬ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ቀረጥ ለማስነሳት ጥረት እየተደረገ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በጥሬ ቆዳና ሌጦ ዘርፍ ላይ የተጣለውን ቀረጥ በማስነሳት ለውጭ ገበያዎችም እንዲቀርብ ለማድረግ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የስጋ፣ ቆዳና ሌጦ ዘርፍ ዴስክ ኃላፊ አስመላሽ በርሄ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ዘርፍ ላይ የተጣለው ቀረጥ እንዲነሳ በማድረግ ነጋዴዎች ለሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያዎችም እንዲያቀርቡ ጥረት እየተደረገ ነው።

በአሁኑ ወቅት በገበያ ላይ ጥሬ ቆዳና ሌጦ የሚሸጥበት ዋጋ አትራፊ ባለመሆኑ የተለያዩ አማራጭ ገበያዎችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ የዋጋው መውደቅ ለዘርፉ ትልቅ መሰናክል እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል።

የተጣለው ቀረጥ ሲነሳ በዘርፉ ላይ የሚገኙ ነጋዴዎች አዲስ የገበያ አማራጭ በማግኘት ወደ ውጭ በመላክ ጥሬ ቆዳና ሌጦ እንዳይባክን እና ዋጋው እንዲሻሻል እንደሚያግዝ አመልክተው፤ ይህም ለዘርፉ ትልቅ መነቃቃትን የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አስመላሽ ገለጻ፤ሻጩ የተሻለ ዋጋ ስለማያገኝበት የጥሬ ቆዳና ሌጦ በጥራት ተዘጋጅቶ ወደሚፈለግበት ቦታ ለማድረስ በእርድ ወቅት ቆዳን በጥንቃቄ እየገፈፈና እያቀረበ አይደለም። እንዲሁም ገበያው ከመቀዛቀዙ ጋር ተያይዞ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ነጋዴዎች ከዘርፉ እየወጡ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አዋጅ መስተካከል እንዳለበት ባለድርሻ አካላት ያቀረቡት ጥያቄ እንዳለ ያነሱት ዴስክ ኃላፊው፤ አዋጁን ለማስተካከል በቴክኒክና በኢስትሪም ኮሚቴ ደረጃ ኮሚቴ ተዋቅሮ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነ ተናግረዋል።

አቶ አስመላሽ፤ ፋብሪካዎች ቆዳን አዘጋጅቶና አምርቶ (ፕሮሰስ) ለገበያ ለማቅረብ የሚያግዙ ኬሚካሎችንና የተለያዩ ግብዓቶች ከውጭ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት እያጋጠማቸው ነው።ይህም የሚቀበሉት ጥሬ ቆዳና ሌጦ ማምረት ከሚችሉበት አቅም በታች መሆኑንም ጠቁመዋል።

የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ማህበራት ሁሌም የሚያነሱት ችግር የጨውና የተለያዩ ኬሚካሎች እጥረት እንዳለ ነው የሚሉት ዴስክ ኃላፊው፤ ዘርፉን ለማነቃቃት መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት ስለሆነ አቅራቢ ማህበራቱ ዋጋው ወድቋል በሚል ምክንያት ከገበያው ከመውጣት ይልቅ አዳዲስ ፋብሪካዎች ወደ ዘርፉ እየገቡ በመሆኑ በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባ አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለዘላቂ ሰላም ከብሔራዊ ምክክሩ የተሻለ አማራጭ የለም!

የሰላም እጦት ሊያስከፍል ስለሚችለው ያልተገባ ዋጋ ከኛ ከኢትዮጵያውያን በላይ ሊመሰክር የሚችል አለ ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ በዘመናት ውስጥ ዋጋ ያልከፈለ ትውልድ የለም ብሎ ለመናገር በሚያስደፍር የታሪክ ትርክት ውስጥ ያለን ሕዝቦች ነን። ይህ እንደ ጥላ የሚከተለን ችግር ዛሬም ያለውን ትውልድ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እያስከፈለው ይገኛል።

ለዘመናት ላለንበት ድህነት እና ኋላቀርነት ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ይህ ሀገራዊ የሰላም እጦት ፤ በቀደመው ዘመን ከነበርንበት ከፍያለ የስልጣኔ ማማ አውርዶናል፤ በየዘመኑ ወደዚያ ማማ ለመመለስ የምናደርገውን ሀገራዊ ጥረት እና መነሳሳት ትርጉም ያለው ውጤት እንዳይኖረው በማድረግ በተስፋ ቁዘማ ውስጥ እንድንኖር አስገድዶናል።

የሰላም እጦት ችግራችንን በአግባቡ ለመረዳት ፈቃድ ማጣታችን፣ በችግሮች ዙሪያ በግልጽ የመነጋገር ባህል ማዳበር አለመቻላችን ፣ ከሁሉም በላይ የተለያዩ ፍላጎቶችን አጣጥሞ ማስኬድ የሚያስችል ማህበረሰባዊ የፖለቲካ ባህል አለማዳበራችን በብዙ ስለ ሰላም እየዘመርን ፣ በብዙ የሰላም እጦት ብዙ ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል የተገደድን ሕዝቦች ሆነናል።

ተመሳሳይ ነገር እየተነጋገርን ለመደማመጥ ፈቃደኝነት ከማጣታችን የተነሳ የአንድ ዘመን የረጅም ዘመናት ቅኝት በሚመስል የታሪክ ትርክት እንዲቋጭ ሆኗል።“ቀይ” እና “ነጭ” በሚል የሽብር ትርክት ለሀገር ነገዎች በብዙ ተስፋ የተነቃቃ ትውልድ ትርጉም አልባ ለሆነ መስዋዕትነት ተዳርጓል።

እያንዳንዱ የለውጥ መነቃቃት በአሮጌ /ዘመኑን በማይዋጅ የመናናቅ እና ኃይል አምላኪ የፖለቲካ ባህላችን እየተጠለፈ ፣ ሀገር እንደሀገር በለውጥ ማግስት በግጭት አዙሪት ውስጥ እንድትዳክር ፣ በዚህም ዜጎች የለውጥ ተስፋቸውን ብቻ ሳይሆን ሁለንተናቸውን ባልተገባ መልኩ መስዋእት እንዲያደርጉ የተገደዱበት ሁኔታ በስፋት ተስተውሏል።

በቅርቡ በብዙ መስዋዕትነት ፣ በብዙ እልልታና ሆይታ ፣ በብዙ ተስፋ የተጀመረው ሀገራዊ የለውጥ ንቅናቄ ብዙ ርቀት ሳይጓዝ በተመሳሳይ ፈተና ውስጥ መወደቁ ፣ በዚህም እንደሀገር መላው ሕዝባችን ብዙ ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል እንደተገደደ ፣ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በለውጡ ማግስት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት የተጀመሩ መነቃቃቶች ፣ እንደ አቅመቢስነት መገለጫ ታይተው በይዋጣልን ፉከራ የተጀመሩ ግጭቶች እንደሀገር ብዙ ዋጋ አስከፍለውናል። ሀገርን በዘመናት ባልታየ የግጭት አዙሪት ውስጥ በመክተት ሕዝባችንን ከለውጥ ተስፋው ጋር አጋጭተውታል።

ይህ እንደ ሀገር ከትናንት የጥፋት ታሪኮቻችን ቆም ብለን ለመማር የሚያስችል ማህበረሰባዊ ማንነት መፍጠር ካለመቻላችን የመነጨ ችግራችን ዛሬ ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ እየፈተነን ያልተገባ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል። ድንገትም ዛሬ ላይ እውነታውን በአግባቡ ለመገንዘብ የሚያስችል ፈቃደኝነት ካጣን ነገዎቻችንን ተስፋ አልባ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ይታመናል።

ብዙ ፍላጎቶች እና ፍላጎቶች የወለዷቸው ጽንፈኛ አመለካከቶች ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ ስጋት እየሆኑ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶቹና ጽንፈኛ አመለካከቶች ሊያስከፍሉ የሚችለውን ያልተገባ ዋጋ ለመከላከ፣ ከሁሉም በላይ ዜጎች በችግሮቻቸው ዙሪያ በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብለው የሚነጋገሩበትን አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ ነው።

ለዚህ ደግሞ አሁን ከጀመርነው ብሄራዊ ምክክር የተሻለ ዕድል ሊኖር አይችልም ፤ ይችላል ብሎ ማሰብ አንድም የችግሮቻችንን መሠረታዊ ምክንያት በአግባቡ ካለመረዳት ፣ ከዚያም በላይ ዘላቂ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለውን መንገድ ካለማጤን የሚመነጭ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ትልቅ ስህተት ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መዲናዋን ከትምባሆ ጭስ ለመታደግ

ስሜነህ ደስታ

በትምባሆ ውስጥ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ያሉ ሲሆን፤ ዋናውና የማነቃቃት ኃይል ያለው ኒኮቲን (Nicotine) ይባላል። ከዚህ በተጨማሪ ታር (Tar) የሚባል ዝቃጭ ነገር የሚገኝበት ሲሆን፤ በዚህም ውስጥ እስከ 4000 የሚደርሱ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ከ250 የማያንሱት ለሰው ልጅ ጎጂዎች ሲሆኑ፤ 50 የሚሆኑት ለካንሰር በሽታ ያጋልጣሉ። በተለይ አርሰኒክ (Arsenic) እና ቤንዞፕሪን (Benzoprine) የሚባሉት ንጥረ ነገሮች ዋና ካንሰር አምጪ ንጥረ ነገሮች ናቸው።

በዚህም ትምባሆ የሚያስከትለው ውስብስብ ችግር ዓለም አቀፍ አጀንዳ ከሆነ ረጅም ዓመታት አስቆጥሯል። በዓለማችን በየዓመቱ ከስምንት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በትምባሆ ሕይወታቸውን ያጣሉ። ከዚህ ውስጥ ደግሞ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን የሚሆኑት ከአጫሽ ሰዎች በሚመነጭ ጭስ ሕይወታቸውን የሚያጡ መሆኑ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል። በኢትዮጵያም በየዓመቱ ከ16,800 በላይ ሰዎች በትምባሆ ጭስ ምክንያት ለህልፈት እንደሚዳረጉ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን መረጃ ያመላክታል።

በኢትዮጵያ በ2022 በተደረገው ሀገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናት 12 ነጥብ 3 በመቶ ሰዎች ብቻ ከትምባሆ ጭስ ነፃ በሆነ አካባቢ ይኖራሉ። በአንጻሩ 87 ነጥብ 7 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ በተለያየ መንገድ ለትምባሆ ጭስ ተጋላጭ መሆናቸውን ከባለስልጣኑ የተገኘ መረጃ ያሳያል። ይህንን የዜጎችን ተጋላጭነት ለመቀነስ “አዲስ አበባን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ኢንሼቲቭ” በይፋ ሚያዚያ 2013 ዓ.ም ተቋቁሞ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛል።

ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ሕዝብ በሚሰበሰቡባቸው አካባቢዎች ማለትም መዝናኛ ቦታዎች፣ ሲኒማ ቤቶች፣ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ... ወዘተ ሲጋራ የማይጨስባቸው እንዲሆኑ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተሠርተዋል። ለምግብና መጠጥ ተቋማት፣ ለትምባሆ ምርት አከፋፋዮች፣ ለሸቀጣ ሸቀጥ ባለቤቶች እና ለሱቅ በደረቴ አዟሪዎች እንዲሁም ለተለያዩ የኅብረተሰብ ተወካዮች፣ ለተማሪዎች እና የትምህርት ማህበረሰብ ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል። በተለያዩ መገናኛ ብዙኀን በቀጥታ ሥርጭት እና በተለያየ መንገድ የሚገለጽ የሚዲያ ሽፋን ተሠርቷል። ታትመው የተሰራጩ የህትመት ውጤቶችም አሉ።

ከቁጥጥርና ክትትል ሥራ አንጻር ደግሞ በልዩ ሁኔታ ከሲቪክ ማህበራት ጋር በመተባበር በምግብና መጠጥ ተቋማት የቀንና የማታ የትምባሆ ቁጥጥር ሥራ ተሠርቷል። የድንገተኛ ምልከታም ተደርጓል። በዚህ ክንውን በተገኙ ግኝቶች መጠን የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ቤቶቹን እስከማሸግና ከፖሊስ ጋር በመተባበር ክስ እስከ መመስረት ተከናውኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን መረጃ እንደሚያሳየው፣ በዚህ ተግባር የመጡ ተስፋ ሰጪ ለውጦች አሉ። በአዋጅ 1112/2011 የተቀመጡ ክልከላዎችን የንግድ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፣ የኅብረተሰቡ የትምባሆ ቁጥጥር ባለቤትነት መጨመሩ፣ ጥቆማዎችና አስተያየቶች በባለቤትነት ስሜት የሚሰጡ ዜጎች መበራከታቸው፣ ከትምባሆ ጭስ ነፃ የሆኑ ተቋማት መበራከታቸው (ከነበረበት 42 በመቶ ወደ 75 በመቶ አካባቢ መድረሱ) እንዲሁም ሞዴል ተቋማት ቁጥራቸው መጨመሩን (ከ240 በላይ ባርና ሬስቶራንት እንዲሁም ከ2000 በላይ ሱቆች) ያስረዳል።

ይሁን እንጂ የግንዛቤ ማስረጽም ሆነ የቁጥጥርና የእርምጃ ሥራው ልክ ኢንሼቲቩ ሲጀመር እንደነበረው ተጠናክሮ ባለመቀጠሉ፤ አሁንም ክልከላ በሚደረግባቸው ቦታዎች ሙሉ በሙሉ ሲጋራ እንዳይጨስ ማድረግ አልተቻለም። ባለሱቆችም በፍሬ አንሸጥም ብለው ደንበኛ አይመልሱም፤ አጫሾችም በፍሬ ለመግዛት እና ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ለማጨስ ሲሳቀቁ አይስተዋሉም። ማህበረሰቡም አጫሾች በተከለከለ ቦታ ሲያጨሱ ተቆጣጣሪ አካላትን ሳይጠብቅ ለምን ብሎ ከማስቆም አንጻር አሁንም ሰፊ ክፍተት ይስተዋላል።

**ትምባሆ የሚያስከትለው ውስብስብ ችግር ዓለም አቀፍ አጀንዳ ከሆነ ረጅም ዓመታት አስቆጥሯል። በዓለማችን በየዓመቱ ከስምንት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በትምባሆ ሕይወታቸውን ያጣሉ**

ስለዚህ አሁን አሁን አዲስ አበባን ከትምባሆ ጭስ የመታደግ እንቅስቃሴ ሥራው እንደአጀማመሩ አለመሆኑን፤ ኢንሼቲቩን በበላይነት የሚያስተባብረው ከንቲባ ጽህፈት ቤቱ እራሱ የማያስተባብለው ሀቅ ነው። ስለሆነም በቀጣይ ምን ቢሠራ መልካም ነው የሚለው ላይ የግሌን አስተያየት እንደሚከተለው እሰነዝራለሁ።

ይኸውም፣ ግንቦት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ‹‹ሕፃናትን ከትምባሆ ኢንዱስትሪ ጣልቃ ገብነት እንከላከል›› በሚል መሪ ቃል ለሚከበረው የፀረ ትምባሆ ቀን የተለያዩ የንቅናቄ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። እነዚህ የንቅናቄ ሥራዎች ዕለቱ ከተከበረ በኋላም በዚያው እንዲቀጥሉ ማድረግ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ የግንዛቤ ማስረጽ፣ የቁጥጥር እና የእርምጃ አወሳሰዱን የሚያግዙ ተግባራትን በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል።

ይህን ተግባር ያዝ ለቀቅ በማድረግ ሳይሆን አጫሾች የሚያጨሱበት ቦታ አጥተው እስኪቸገሩ ድረስ፤ አጫሾች በፍሬ የሚሸጥላቸው አጥተው ማጨሳቸውን እንዲያዘገዩ እስከማድረግ ድረስ፤ ከተቻለ ደግሞ ማጨሳቸውን እስኪያቆሙ ድረስ ሥራዎችን መሥራት ይገባል እላለሁ።

ለዚህ ተግባር ደግሞ የከተማው ሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ስለሆነ በተለያዩ አደረጃጀቶችና አማራጮች ኅብረተሰቡም አጋዥ እንዲሆን የግንዛቤ ማስረጽ ሥራ መሥራት ይገባል። "ማጨስ ክልክል ነው" የሚለው ማስታወቂያም በተገቢ ቦታዎች ሁሉ ቢለጠፉ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 150/2015 እንዲያስፈጽማቸው ከተሰጡት ለደንብ መተላለፎች የወጡ የቅጣት ሰንጠረዦች ላይ አዋኪ ድርጊትና መሰል ተግባራትን መፈጸም በሚለው ስር ጫት መቃምና ሺሻ ማጨስ ተካቷል። ይሁን እንጂ ስለ ሲጋራ ማጨስ የተባለ ነገር ስለሌለ የደንብ ማስከበር ኦፊሰሮች እርምጃ ለመውሰድ ሲቸገሩ ይስተዋላል። ስለሆነም በቀጣይ እንደ ጫቱና ሺሻው ሁሉ በአዋጁ ሲጋራ ማጨስ በደንብ መተላለፍ የሚካተትበት ሁኔታ ተፈጥሮ የደንብ ማስከበር ኦፊሰሮች ቁጥጥርና እርምጃ የሚወስዱበት አግባብ ሊፈጠር ይገባል።

ሌላው ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ እና የአዲስ አበባ ከተማ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ሲጋራ ማጨስን በተመለከተ የሚያሳዩትን የተለያየ ሃሳብ አጥብበው አንድ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህ የተለያየ ሃሳብ የሚከተለውን ይመስላል፤ ቢሮ ሆቴሎችና መሰል ተቋማት ለአጫሾች ለብቻቸው የተከለለ ቦታ እንዲዘጋጁላቸው ተደርጎ ያጭሱ የሚል አቋም አለው። ባለስልጣኑ ደግሞ የዜጎችን ተጋላጭነት ለመቀነስ በሆቴሎችና መሰል የመዝናኛ ቦታዎች በግቢው ውስጥም ሆነ ከግቢው ውጭ ሰው ባለበት አስር ሜትር ራዲያስ ውስጥ ማጨስ አይፈቀድም ይላል። ይሄን ልዩነት በአጭር ጊዜ ተቋማቱ ማጥበብና የደረሱበትን ውሳኔ ለሆቴሎችና መሰል ተቋማት ማሳወቅ ይገባቸዋል።


እንደእኔ አስተያየት የባለስልጣኑን ሃሳብ እደግፋለሁ። ምክንያቱም አጫሾች የሚያጨሱበት ቦታ ሲያጡ የሚያጨሱት መጠን ይቀንሳል። በዚህም የዜጎች ተጋላጭነት ቁጥር ይቀንሳል። መዲናዋን ከትምባሆ ጭስ የፀዳች ለማድረግ አንድ ዜዴ ነው። ስለሆነም እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራት ቀጣይነት ባለው መንገድ በትብብር የሚተገበር ከሆነ መዲናዋን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ማድረግ ይቻላል ባይ ነኝ።

ዜና

# ፈተናውን በብይነመረብ ለመስጠት መታቀዱ ኩረጃን ለማስቀረት ዘላቂ መፍትሔ ነው

## -የ12ኛ ሀገር አቀፍ ፈተናን ለመፈተን ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**




አዲስ አበባ፡- የ12ኛ ሀገር አቀፍ ፈተናን በብይነመረብ ለመስጠት መታሰቡ ኩረጃንና የፈተና ስርቆትን ለማስቀረት ዘላቂ መፍትሔ ነው ሲል የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት አስታወቀ፡፡ የ2016 የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በብይነ መረብና በወረቀት ለመፈተን ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ ነው ሲልም ተናግሯል፡፡

የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር እሸቱ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በብይነመረብ ለመስጠት መታቀዱ ኩረጃንና የፈተና ስርቆትን ለማስቀረት ዘላቂ መፍትሔ ነው፡፡

በ2016 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በብይነመረብና በወረቀት በመፈተን የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የ12ኛ ሀገር አቀፍ ፈተናን በብይነመረብ መስጠት ኩረጃንና ስርቆት በዘላቂነት ለመፍታት አስፈላጊ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ፈተናውን ለተወሰኑ ተማሪዎች በብይነመረብ የመፈተን ሥራ በተያዘው ዓመት ይጀመራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ኤጀንሲ የፈተና ስርቆትና ኩረጃ ትልቁና የረጅም ጊዜ ችግሩ ሆኖ ቆይቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ፈተናውን በብይነመረብ የመስጠት ሥራ ተጀምሯል፤ በሂደትም ሙሉ ለሙሉ የወረቀት ፈተናው ይቀራል ብለዋል፡፡

የ2016ዓ.ም የ12ኛ ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና በብይነመረብ መሰጠት መጀመሩ የመጀመሪያ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ተጋዳሮቶች ይገጥሙታል ተብሎ መታሰቡን አመልክተው፤ የሚገጥሙ ችግሮችን ፈትቶ ያለምንም ችግር ፈተናውን ለመስጠት ከወዲሁ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ፈተናውን በሚወስዱ ተማሪዎችና ፈተናውን በሚሰጡ ፈታኞች ያለው የብይነመረብ ክህሎት ክፍተት፤ የኤሌክትሪክ ኃይልና የኢንተርኔት መቆራረጥ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት እጥረትና ድጋፍ የሚያደርጉ የሰው ኃይል በቂ አለመሆን ያጋጥማሉ ተብለው የተለዩ ችግሮች ናቸው ያሉት ዶክተር እሸቱ፤ ችግሮችን ለመፍታት ተፈታኞችንና ፈታኞችን የማለማመድ፤ ጀኔረተሮችን የማዘጋጀት፤ ከቴሌ ጋር የመሥራት፣ ለድጋፍ ሰጪዎች ስልጠና በመስጠት ቁጥራቸውን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የብይነመረብ ፈተናው ቀድሞ ኮምፒውተሮችና መሠረተ ልማቶች በተዘረጉባቸው ከተሞች በሚገኙ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጥ መሆኑን ገልጸው፤ ተማሪዎች ከመኖሪያ ቤታቸው በመመላለስ ፈተናውን ይወስዳሉ ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር እሸቱ ገለጻ፤ የ2016 የ12ኛ ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና በወረቀትና በብይነመረብ ለመስጠት ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ ነው፤ ስለፈተናውና ስለፈተና አሰጣጡ ለተማሪዎች መረጃ ተደራሽ ማድረግ፤ ክልሎች ያላቸውን የተፈታኝ ብዛት እንዲለዩና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ፤ ለብይነመረብ ተፈታኞችና ፈታኞች ስልጠና መስጠትና ግብአት ማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ከፍተኛ ዝግጅትም እየተደረገ ነው፡፡

ኩረጃንና ፈተና ስርቆትን የትምህርት ጥራት ከመጉዳት ባለፈ የተማሪዎችን የመመራመር ፣ በራስ የመተማመን፣ የማብሰልሰል፣ በትምህርት ውስጥ መማር የሚባለውን የባህሪ ለውጥ እንዳያዳብሩ የሚያደርግ ትልቅ እንቅፋት ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ችግሩን በመሻገር የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ሰፊ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

# ኮሚሽኑ ፈተና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አካታችና አሳታፊ ወደሆነው የዝግጅት ምዕራፍ ማገባደጃና የምክክር ሂደት መግቢያና አጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ ማብሰሪያ ሂደት እንኳን አደረሳችሁ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ፈተናዎች ቢገጥሙትም ፈተናዎቹ ሳይበግሩት ብዙዎች ሲመኙት የነበረውን መቀራረብንና መግባባትን ለማምጣት ሥራውን እያከናወነ ለዚህ ደረጃ መብቃቱን ተናግረዋል፡፡

በዚህም ኮሚሽኑ እስካሁን በአስር ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች ከ1ሺ በላይ በሚሆኑ ወረዳዎች በአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ሂደት የሚሳተፉ ተወካዮችን በማስመረጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጀንዳ መሰብሰብ ሥራውን እንደጀመረ አክለዋል፡፡

በቀጣይ ልክ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁሉ የተሳታፊዎች መረጣ በተካሄደባቸው ክልሎችና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አጀንዳ እንደሚሰበስብ የጠቆሙት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በአማራና በትግራይ ክልሎች ደግሞ የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ እንደሚያካሂድ ተናግረዋል፡፡

የአሁኑ ወጣት ትውልድ ከቀደሙት ትውልዶች ብዙ ተምሮ የተሻለ የሰላምና የእድገት ውርስ ይተዋል የሚል እምነት ኮሚሽኑ እንዳለውም አክለዋል፡፡

ከስብራት ሕይወት ወጥተን ወደ ተሻለ ሕይወት እንሸጋገር ዘንድ ወጣቱ ችግሩን በአጀንዳ ቀረፃ ጠብመንጃውን ወደ ሃሳብ መንጃና ማንሸራሸሪያ እንዲቀይር ኮሚሽኑ በትህትና ይጠይቃል ብለዋል፡፡

የሀገራችን ችግር ወደ ሀገራዊ መፍትሔ ለማምጣት ኮሚሽኑ በምክክር ሂደት የሰላም በር በየትኛውም ቦታ ላሉ ወገኖች እንዲመቻች ጠንክሮ እንደሚሠራም ዋና ኮሚሽነሩ አረጋግጠዋል፡፡

በተጀመረው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አጀንዳውን በግልም ሆነ በጋራ ወደ ኮሚሽኑ ማምጣት እንደሚችል የጠቆሙት ዋና ኮሚሽነሩ፤ ምክክሩ አካታች እንደሚሆንና ሂደቱም ግልፅና ተዓማኒ በሆነ መልኩ እንደሚከወን በንግግራቸው አረጋግጠዋል፡፡

የሀገራቸው ሰላም እና እድገት አሳስቧቸው የምክክሩ ሂደት እንዲሳካ ኮሚሽኑን እያገዙ ላሉ ሁሉ የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ር) በኮሚሽኑ ስም ምስጋና ማቅረባቸውን የኮሚሽኑ መረጃ ያመለክታል።

SNRS HCACAD NEWS

## ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የቤት ፍላጎትን ለማሟላት የተቀየሰው የአስተዳደሩ ስትራቴጂ



ቤት ሰዎች የሚጠለሉበት ብቻ ሳይሆን ገመና ሸፋኝ ምስጢር ደባቂም ጭምር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በከተሞች ውስጥ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መኖሪያ ቤት ለማግኘት እጅግ በጣም መቸገራቸው ግልጽ ነው፡፡ በተለይም በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በየጊዜው እየጨመረ ከመጣው ከኑሮ ውድነት ጋር ተደማምሮ ሕይወትን ፈታኝ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም በክልል ከተሞች የቤት ኪራይ በየጊዜው እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ በመንግሥት ሥራ የሚተዳደሩትን ሠራተኞች አቅም ያላገናዘበ ስለሆነ ነገሩን ከባድ አድርጎታል፡፡

መንግሥትም ከከተማ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመሬት አቅርቦቱ እየጠበበ ስለመጣ ዜጎች በውስን መሬት በማህበር ተደራጅተው ገንዘብ ቆጥበው መኖሪያ ቤት እንዲሠሩ እያደረገ ነው፡፡ በከተማ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ከተጠቃሚው አቅምና ከከተማ ዕድገት ጋር መጣጣም ባለመቻሉ ይህንን ችግር ለማቃለል መንግሥት በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የሀዋሳ ከተማ አስተዳደርም የነዋሪውን የቤት ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከስትራቴጂዎቹ ውስጥ አንዱ ነዋሪውን በማህበር በማደራጀት መኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ማቅረብ ሲሆን፤ ላለፉት ዓመታትም ቤት ፈላጊዎችን በማህበር አደራጅቶ መሬት በመስጠት የቤት ባለቤት አድርጓል፡፡ በዚህ ዓመትም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ የሀዋሳ ከተማ እያስመዘገበች ካለችው ፈጣን እድገት አንፃር የመኖሪያ ቤት ፍላጎቱን ተደራሽ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገም ነው፡፡

የቤት ግንባታ ስትራቴጂው የከተማዋን ውበትና ዕድገት ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፤ በቁጠባ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችም እንደ ከተማ የተቀመጡ የቤት ግንባታ ስትራቴጂዎችን ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም በቤት ፍላጎት አማራጭ ተጠቃሚ የሚሆኑ በማህበር የተደራጁ አካላት በቤት ልማት አማራጩ ተሳታፊ መሆን የሚያስችላቸውን የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት የሚጠበቅባቸውን 50 በመቶ እና ከዚያም በላይ መቆጠብ ይኖርባቸዋል ነው የተባለው።

በዚህ ረገድ የከተማዋ አስተዳደር የቤት ፍላጎት አቅርቦትና አማራጭን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂን ተግባራዊ ለማድረግ በደንብ ቁጥር 03/2015 በክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ፀድቆ ወደ ሥራ መግባት ተችሏል።

በዚህም መሠረት የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የቤት ፍላጎት አቅርቦትን ለማሻሻል በሚል ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ ይህም በከተማዋ ተገቢውን የቤት መሥሪያ አቅምን 50 በመቶና ከዚያም በላይ የቆጠቡ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን እንዳለበት ተገልጿል። በዚህ ረገድ መኖሪያ ቤት ለመሥራት በማህበር ተደራጅተው 50 በመቶ እና ከዚያም በላይ የቆጠቡ 35 ማህበራትም በመኖራቸው የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ለመስጠት ከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ ላይ ደርሷል።

በከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ የተቋቋመው የስትሪንግ ኮሚቴ በከተማዋ ያለውን የቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠንን እንደ ችግር በመገምገም በማህበር ለተደራጁ 50 በመቶና ከዚያም በላይ ገንዘብ ቆጥበው ላጠናቀቁ ማህበራት የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ለመስጠት የወሰነው። የመኖሪያ ቤት አማራጭና አቅርቦት ስትራቴጂን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሚሰጠው ይህ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ በከተማዋ ያለውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ሊያቃልል የሚያስችል እንደሆነም ተጠቁሟል።

የመኖሪያ ቤት ግንባታ የሚሰጣቸው ለቤት መሥሪያ የሚውል ተገቢውን ቁጠባ የፈፀሙ የመንግሥት ሠራተኞች፣ መምህራን፣ የጤና ባለሙያዎች፣ የተሰናበቱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች መሆናቸውም ታውቋል። በከተማዋ ውስጥ ባለፉት ጊዜያት በማህበር ተደራጅተው ለቤት መሥሪያ የቆጠቡ 64 ማህበራት መኖራቸው የተገለጸ ሲሆን፤ 471 ሚሊዮን 207 ሺህ ብር መቆጠብ እንደቻሉ ተገልጿል። ከእነዚህ ማህበራት ውስጥ 50 በመቶ እና ከዚያም በላይ የቆጠቡ 35 ማህበራት 378 ሚሊዮን ብር በመቆጠባቸው የመኖሪያ ቤት ግንባታ መሬት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ መሆናቸውን ከተማ አስተዳደሩ አስታውቋል።

ሃምሳ በመቶ እና ከዚያም በላይ የቆጠቡ ማህበራት ቁጠባቸውን የብድር አቅርቦቱን ለሚያመቻቸው የሲዳማ ባንክ ሂሳባቸውን ማዞር የቻሉ ስለመሆናቸውም አስተዳደሩ ባደረገው የስትሪንግ ኮሚቴ ውይይት ወቅት ገልጿል። ለእነዚህ 35 ማህበራት በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ከተማ አስተዳደር በማህበር ለተደራጁ አካላት የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ርክክብ ለማድረግ ወስኗል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## በአረንጓዴ አብዮት ሒደት

በአለማችን ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ጋር ከተያያዙ ኩባንያዎች በማስከተል ኢኮኖሚውን ይመራል ተብሎ የሚጠበቀው ግብርና ዘርፍ ነው።ቻይናንና ሕንድን ጨምሮ የበርካታ ሀገራት ዜጎች መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ጎራ መቀላቀል የምግብ ፍላጎትን በብዙ እጥፍ ስለሚያሳድገው እና በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የግብርና ምርት እየተዛባ መሆን፤አረንጓዴ አሻራንና የግብርና ምርታማነትን መሳ ለመሳ ለምታካሂደው ሀገራችን ጥሩ አጋጣሚ ነው።በተለይ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት መጨመር ብንችል በኢኮኖሚያችን ላይ መዋቅራዊ ለውጥ የማምጣት እምቅ አቅም አለው።ሰፊ መሬትና ከአመት እስከ አመት የሚገማሸሩ ወንዞች፤ለግብርና ምቹ የአየር ንብረትና ወጣት አምራች ኃይል ላላት ሀገር ግብርናን መሠረት አድርጋ አብዮት ማካሄዷ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሦስት ሚሊዮን 385 ሺህ 137 የግብርና ማሽነሪዎች ከቀረጥና ከታክስ ነጻ ወደ ሀገር እንዲገቡ መደረጉን፤ማሽነሪዎችን ከማስገባት ጎን ለጎን የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም የማጠናከር ሥራ መከናወኑን ወዲህ ሳነብ፤በሌላ በኩል በ2016 የስንዴ ምርትን ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ባለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እስከ ግንቦት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ99 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰቡን፤በሁሉም ክልሎች በ2016 በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ሳጤን፤በሌላ ገጽ ለአረንጓዴ አሻራ የተሰጠውን ትኩረት እንዲህ ስመለከተ ሀገር አረንጓዴ አብዮት ላይ መሆኗን አረጋገጥሁ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ፤አረንጓዴ አሻራ ለኢትዮያውያን እንደ ባህል እስኪቆጠር ተግተን በመሥራት አረንጓዴ የለበሰች ኢትዮጵያን እውን አናደርጋለን ብሎናል።ለእኔ "አረንጓዴ አሻራ" ባህል ከማድረግም ሆነ ሀገርን አረንጓዴ ከማልበስ የተሻገረ ነው።ሀገርን ከድህነትና ኋላቀርነት በአንድነት ይዞ የሚነሳ፣ከተረጅነትና ከተመጽዋችነት በማላቀቅ ነጻነቷንና ሉዓላዊነቷን ሙሉኡ የሚያደርግ፤ወዘተረፈ ስለሆነ ችግኝ ተከላን ባህል ከማድረግም ሆነ ሀገርን አረንጓዴ ከማልበስ በከባዱ የተሻገረ ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት በተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች በመጀመሪያው ምዕራፍ ከ32 ቢሊየን በላይ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን የተተከሉት ችግኞችም በዘርፉ ሙያተኞች በተደረጉት ክትትል 90 በመቶ ለመፅደቅ ችለዋል፡፡የተፈጥሮ ሃብትና የሕይወታዊ ሃብት ጥበቃ ሥራ ሲጠናከርና ተከታታይነት ባለው መንገድ ሲሰራ ከአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ ነጻ የሆነና መልካምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ያደረገ አካባቢያዊ የአየር ንብረት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ዕድል ይሰጣል፡፡

በመጀመሪያው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በመላ ሃገሪቱ በተተከሉ ችግኞች ቀደም ሲል ተራቁተው የነበሩና የአፈር መሸርሸር አጋጥሟቸው የነበሩ አከባቢዎች በአሁኑ ወቅት ወደ ቀድሞ ገጽታቸው እየተመለሱና መሬቱም እያገገመ መሆኑን የግብርና ባለሙያዎች ምስክርነታቸውን እየሰጡ ነው፡፡የአረንጓዴ አሻራ ሥራችን በተለያዩ ዘርፎች ውጤቶችን እያሳየን ነው፡፡

ተደጋጋሚ ድርቅ ሲያጠቃቸው የነበሩ አካባቢዎች ዝናብ ማግኘት ጀምረዋል፣ የጎርፍ አደጋን ለመቀነስ ተችሏል፣ የደረቁ ምንጮችና ሀይቆች እንደገና ቀድሞ ወደ ነበሩበት መመለስ ችለዋል፣ ለበጋና የመኸር እርሻ ተስማሚ የሆነ ዝናብ ማግኘት ተችሏል፡፡ከሥራ እድል ፈጠራነት አንጻር ለእንስሳት መኖነት፤ ለንብ ማነብ ፤ ለካርቦን ሽያጭና ለጎረቤት ሀገራት መልካም ጉርብትና እና የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በዘንድሮ 2016/17 በ132 ሺህ 144 ችግኝ ጣቢያዎች ለአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብሩ ችግኝ ተዘጋጅቶ 6 ነጥብ 3 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል የቅድመ-ተከላ ዝግጅቶች በሁሉም አካባቢዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ 25 በመቶ የሚሆነው በአባይ ተፋሰሶች የሚተከል ይሆናል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ዝግጅትና ተከላ ለበርካታ ወጣቶችና ሴቶች ሰፊ የስራ እድል እየፈጠረ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

**አረንጓዴ አሻራ ለኢትዮጵያውያን እንደ ባህል እስኪቆጠር ተግተን በመሥራት አረንጓዴ የለበሰች ኢትዮጵያን እውን አናደርጋለን ብሎናል።ለእኔ "አረንጓዴ አሻራ" ባህል ከማድረግም ሆነ ሀገርን አረንጓዴ ከማልበስ የተሻገረ ነው**

በ6 ሺህ 200 ተፋሰሶች የስነ-አካላዊ ስራ በመስራት በስነ-ህይወታዊ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ተግባራት እየተከናወኑ ነው፡፡ በመርሃ ግብሩ ላይ ለተከላ የተዘጋጁ ችግኞች ዘርፈ ብዙ ገቢ የሚያስገኙ አትክልትና ፍራፍሬ፤ ጥምር ደን፤ ለከተሜነት ውበት የሚዉሉ እና ለደን የሚውሉ ናቸዉ፡፡ ለሁለተኛው አረንጓዴ አሻራ ሁለተኛ ዓመት የአረንጓድ አሻራ ስኬት የሁላችንም ተሳትፎና ዝግጁነት ከወዲሁ ይጠበቃል ይለናል የአገልግሎቱ መልዕክት፡፡ወደ ነገረ አብዮት ስመለስ፤

ዓለማችን ከፖለቲካዊ አብዮቶች (መነሻ ቃል፡ አበየ- 'እምቢ አለ') በተጨማሪ ሌሎች ዘመን ቀያሪ፤ ሂደት ለዋጭ አብዮቶችን አስተናግዳለች - የግብርና አብዮት፤ የኢንዱስትሪ አብዮት ፤ የሳይንስ አብዮት፤ የዲጂታል አብዮት። እነዚህ አብዮቶች 'አብዮት' ያሰኛቸው ከዛ በፊት ግብርና ወይም ኢንዱስትሪ ወይም ሳይንስ ወይም ዲጂታላዊ እንቅስቃሴ ወይም ስራ ስላልነበረ አይደለም። በመጠናቸውና በአይነታቸው ከተለመደውና ከነበረው አሰራርና አካሄድ ለየት ባለ መልኩ ሁኔታ ቀያሪ በሆነ መገለጫ ግብርናው፤ ኢንዱስትሪው፤ ሳይንሱና የመረጃ ቴክኖሎጂው ስለተስፋፋና አገሮች ከተለመደው መንገድ 'በእምቢታ' ወጥተው ወደ አዲሱ መንገድ ስለገቡ ነው ከአብዮት ጋር ተያይዞ የሚነገርላቸው። ይሉናል ጌታቸው አሰፋ በአዲስ ጉዳይ ላይ ባስነበቡን ቆየት ባለ መጣጥፋቸው።

ከአንድ ሄክታር ይገኝ የነበረውን የምርት መጠን በከፍተኛ ደረጃ ከማሳደግ ጋር በተያያዘ የተገኘውን የለውጥ እምርታ የግብርና አብዮት እንለዋለን። የግብርና አብዮት በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በተለያየ ወቅት ተካሄዷል። ለምሳሌ በእንግሊዝ ከአስራ አምስተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ ለአራት ክፍለዘመናት ከኢንዱስትሪ አብዮትና ከሳይንስ አብዮት ጋር መነሻና መድረሻ እየሆነ ተከስቷል። በአረቡ ዓለምም ከዚህ በጣም ቀድም ብሎ ከስምንተኛው ክፍለዘመን እስከ አስራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የዘለቀ አብዮት ነበር።

በንጽጽር በቅርቡ በኤዥያና (በተለይ በህንድ) በላቲን አሜሪካ (በዋናነት በሜክሲኮ) የተካሄዱትን የግብርና አብዮቶች ነው አረንጓዴ አብዮት ተብለው የሚጠሩት።በ1960ዎቹ 1970ዎቹ በህንድና ሜክሲኮ የተከሰተውን አረንጓዴ አብዮት እውን እንዲሆን የደገፉ የሮክፌለር ፋውንዴሽን ፤ የፎርድ ፋውንዴሽን እንዲሁም የዓለም ባንክ ነበሩ። እነዚህ ድርጅቶች ይህን አረንጓዴ አብዮት በ1980ዎቹ በአፍሪካም እንዲከሰት ሊያደርጉ ሲሞክሩ የዓለም አቀፍ አካባቢ ተቆርቋሪዎች ተቃውሞ በማሰማታቸው ይህን ድጋፍ ለመስጠት አልፈቀዱም። የተቃውሞው ምንጭ በነዚህ አብዮቶች ተጠቃሚ ለምርት መጨመሩ ግብአት የሚሆኑትን ነገሮች የሚያቀርቡት የምዕራብ አገሮች ትልልቅ ኩባንያዎች ናቸው እንጂ ገበሬው አይደለም የሚል ነው። ጉዳቱ በአካባቢም በዘላቂ ምርታማነትም በኩል ከፍተኛ ነው የሚል ነው።

ይህ ከሆነ ሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ካለፈ በኋላ እነሆ አፍሪካ በተቃውሞው ምክንያት የዘገየው አረንጓዴ አብዮት መፈንጃ ልት ሆን እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ሲጀመር 'አረንጓዴ አብዮት' የሚለው ስም አሳሳች ነው። 'ለምን?' ቢባል ለምሳሌ ይህ ስም 'አረንጓዴ ኢኮኖሚ' ከሚለው ጋር ዝምድና የሌለውና አረንጓዴነቱ ከአካባቢ ተጽእኖ አለመኖር ወይም አነስተኛ መሆን ጋር የማይገናኝ ነው። የስም አወጣጡም አንድ የአሜሪካ ባለስልጣን ንግግር ሲያደርጉ "በነህንድና ሜክሲኮ የተካሄደው አብዮት በሶቭዮት ህብረት የነበረውን ቀይ አብዮት ያይደለ፤ የአረቦች አይነት ነጭ አብዮት ያይደለ አብዮት ነው። ይህን አብዮት አረንጓዴ አብዮት ብየዋለሁ" ያሉትን መነሻ በማድረግ ነው።

ከዛን ጊዜ ጀምሮ የግብርና ምርት መጠን ላይ ከፍተኛ እምርታ ማምጣት 'አረንጓዴ አብዮት' ተብሎ ከመጠራቱ አኳያ ነው አፍሪካ ማካሄድ አለባት የሚባለው የራሷ የግብርና አብዮትም 'የአፍሪካ አረንጓዴ አብዮት' የሚል ስያሜ ያገኘው። ይህ የአፍሪካ አብዮት እውን እንዲሆንም የአፍሪካ መንግሥታት ጥረት የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ እና እንዲሁም የታወቁ ግለሰቦችና ባለጸጎች እንቅስቃሴ እየታየ ነው። ከአዲሱ የአፍሪካ አረንጓዴ የግብርና አብዮት ጀርባ የተከበሩ ሰዎች አሉ- የቀድሞው የመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ ኮፊ አናን እና ቢል ጌትስ የመሳሰሉት።ወደ ሀገራችን ስንመለስ፤

የአገራችን ደጋማው ክፍል ለዘመናት በመታረሱ ምክንያት በሄክታር የሚገኘው ምርት በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ተጨማሪ አዲስ መሬት ወደ ግብርናው እስካልተቀላቀለ ድረስ በቂ ምርት ማግኘት ከባድ ከሆነ ቆይቷል። በየጊዜው ደግሞ ሊጨመር የሚችል አዲስ መሬት ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ካለው መሬት የምናገኘውን ምርት መጨመር የምንችልበት መንገድ መፈለግ የግድ ነው። መንግሥት በግብርና ኤክስቴንሽን ባደረገው ጥረት አበረታች ውጤትም ተገኝቷል። ለምርት መጨመር ምክንያት የሆነው ማዳበሪያን ከውጪ በውጪ ምንዛሪ በማስገባት በመሆኑ ውሎ አድሮ አቅሙ ከተገኘ ሁኔታዎች ከተመቻቹ ማዳበሪያም ሆነ ሌላው የግብርና ግብአት በአገር ውስጥ ማምረት የምንችልበትን እድል መጠቀም ወሳኝ ነበር።

'ምን ያህል መሬት? በምን ያህል መጠን? ለምን ያህል ጊዜ ነው በግብአቶች ጣራ ስር ማዋል ያለብን? ይህን ስናደርግ የሚፈጠሩ የጎንዮሽ ተጽእኖዎች እንዴት ነው የምንመክታቸው? የግብአቶች ምርጥ የአጠቃቀም ባህልስ የምንፈጥረው እንዴት ነው?' የሚሉትን ጥያቄዎች በሁለንተናዊ ግምገማ ስልት የየዘርፉ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው መመለስ አለባቸው።

በዚህ በኩል የህንድ ልምድ በበጎም በመጥፎም ጥሩ መነሻ ሊሆነን ይችላል። 'ህንድ ራሷን መመገብ አትችልም። ከአሁን በኋላ ካላት የህዝብ ብዛት አንጻር መጪው ጊዜ ለህንድ መጥፎ ነው።' ተብሎ በተተነበየ በስድስት ዓመት ውስጥ እድሜ በዋናነት ሩዝ ላይ መሰረት ላደረገ አረንጓዴው አብዮት ራሷን ከመመገብ አልፋም በስፋት ወደ ውጪ ለመላክ በቅታለች። ይህ በጎው ነው። በመጥፎ ጎኑ ደግሞ መጠነ ሰፊና ያልተመረጠ የማዳበሪያና የጸረ ተባይ አጠቃቀም ጋር የሚያያዝ የአረንጓዴ አብዮት ሰርቶ ማሳያ የሆነችው የህንዷ ፑንጃብ ግዛት የታየው እየጨመረ የመጣ የበሽታና (ለምሳሌ ከጸረ ተባይ ጋር የተያያዘ ካንሰር) የአካባቢ ተጽእኖ (የክርሰ ምድር ውኃ ብክለት እና የመሳሰሉት) በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው።

ሌላው ከምርጥ ዘሩ አይነት ጋር የሚያያዝ የጎንዮሽ ጠንቅ አለ። በሩዝም ሆነ በስንዴ ላይ የተደረገው የምርት ጭማሪ እምርታ የተከሰተው በግንዱ ላይ ይውል የነበረው መዋዕለ ህይወት ፍሰት ተቀንሶ ፍሬ መጨመር ላይ እንዲውል በማድረግ ድንክዬ ስንዴና ድንክዬ ሩዝ ግን ከመደበኛው ዝርያ የበለጠ የሚያፈሩ እንዲሁን በማድረግ ነው። ይሁንና ይህ ዘዴ ከምርት ሂደት በኋላ ከፍሬው በተጨማሪ ለሌላም አገልግሎት (ለምሳሌ ለከብት መኖ) የሚውለው አጠቃላይ የቃርሚያ መጠን የሚቀንስ ነው።

ይህ ደግሞ እኛን በመሳሰሉ አገሮች ከጠቅላላ የቃርሚያ መጠኑ ያገኙት የነበረው ጥቅም ያሳንስብናል። በዛ ላይ ደግሞ እነዚህ ምርጥ ዘሮች ከፍተኛ የማዳበሪያ፤ የውኃ እና የጸረ ተባይ ግብአት የሚጠይቁ ናቸው። እንዲያውም በቂ ግብአት ካላገኙ ከመደበኛ ዘሮች ያነሰ ምርት ነው የሚሰጡት። ይህ ጉዳት ነው። እንደዛም ሆኖ ግን 'የተመረጠውና አዛላቂ የሆነው መንገድ የትኛው ነው?' ብለን የአጭሩንና የረጅሙን ዘመን ተግዳሮቶችንና ጸጋዎችን ለማጣጣም ከአሁኑ ማሰብና ማሰላሰል ይጠበቅብናል። ይህ ሲሆን በአገራችን አሁን ያሉት በጎ ጅምሮች ባለ-ብዙ ዘርፍ አብዮት የማምጣት እድላቸውን ሰፊ ማድረግ እንችላለን ይሉናል ጸሐፊው።

ሻሎም ! አሜን።

# ለግማሽ ክፍለ ዘመን የዘለቀ በጎነት



ፎቶ- ገብሩ ገብሬ

አንዳንድ ሰዎች ለበጎ ስራ የተፈጠሩ ናቸው። ከተወለዱባት ቅጽበት ጀምሮ ይህቺን አለም በመልካም ባህሪና ተግባራቸው የሚፈውሱና የዚህች አለም ገጸ በረከት ተደርገው የሚወሰዱ ሰዎች ጥቂትም ቢሆኑ በየአካባቢው አሉ።የዛሬው የድሬደዋ በጎነት ተምሳሌት ወ/ሮ አሰገደች አስፋው ለዚህ አባባላችን አብነት የሚሆኑ ናቸው።

ወይዘሮ አሰገደች አስፋው የ90 አመት አረጋዊ ናቸው። የዕድሜያቸውን ዕኩሌታ ያሳለፉት ነድያንን እና አረጋውያንን በመንከባከብ ነው። ከልጅነታቸው ጀምሮ ሰዎችን መርዳት ይወዱ ነበር። በኋላም አድገው የራሳቸውን ኑሮ ሲመሰርቱ ነዳያንን በቤታቸው እያስጠጉ መርዳት ጀመሩ። የትዳር አጋራቸው በሞት ሲለዩዋቸውና ልጆቻቸውም ራሳቸውን እየቻሉ ከቤት ሲወጡ፣ ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ለበጎ አድራጎት ስራ ሠጡ።ከ50 አመታት ላላነሰ ጊዜ በጎ እያደረጉ ለብዙዎች መከታ መሆን ቻሉ።

ወይዘሮ አሰገደች አስፋው የዕድሜያቸውን ዕኩሌታ ለከፈሉበት የበጎ አድራጎት ስራቸው ከድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል። እናት ባንክ ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ በስማቸው አንድ ቅርንጫፍ ሰይሞላቸዋል።

## ለብዙዎች መከታ የሆነው ተቋም

በእኒህ ብርቱ ሰው የተቋቋመው ድርጅት አሰገደች የአረጋውያን ማቋቋሚያና መንከባከቢያ ይባላል። በድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያውና አንጋፋ ድርጅት ነው። ዶክተር አሰገደች ህይወታቸውን ሙሉ ለዚህ ድርጅት መስዋዕት አድርገዋል።የተመሰረተውም የዛሬ 30 አመት አካባቢ ነው። አካባቢውን በቅርብ የሚያውቁ ሰዎች እንደሚናገሩት አሁን ድርጅቱ ያለበት ሰፈር ከዚህ ቀደም ጫካ የነበረ ነው። ሰፈሩን በማስተካከል ለአረጋውያን ምቹ እንዲሆን ያደረጉት ወ/ሮ አሰገደች ናቸው።

ወ/ሮ አሰገደች ይህንን የአረጋውያን ማቋቋሚያና መንከባከቢያ ድርጅቱ ከማቋቋማቸው በፊት አረጋውያንን ይረዱ የነበሩት በወላጅ አባታቸው ቤት ነበር።ከዚሁ ጎን ለጎንም በየሆስፒታሉ እየሄዱ የታመሙ ሰዎችን ያጽናኑ ነበር።

የወ/ሮ አሰገደች ልጅ የሆነችው ወይዘሮ እመቤት፤ እንደምትናገረው ወ/ሮ አሰገደች ገና ከጅምሩ ሁለት አላማ ነበራቸው። የመጀመሪያው አረጋውያንን መሰብሰብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በድሬዳዋ ከተማ አገልግሎት ሰጥተው ሜዳ ላይ የሚጣሉ ፈረሶችን ሰብስበው ከአደጋ የመከለል አላማ ነበራቸው። ነገር ግን ከጎረቤት ጋር በዚህ ጉዳይ መስማማት ስላልቻሉ ፈረሶችን የመሰብሰቡ ነገር አልተሳካላቸውም።

ወይዘሮ እመቤት እንደምትናገረው ወ/ሮ አሰገደች ሥራውን የጀመሩት በእናትና በአባታቸው መኖሪያ ቤት ነው።ያለምንም የኃይማኖትና የዘር ልዩነት የተቸገሩ አረጋውያንን ከመንገድ በማንሳት ለብዙዎች አለኝታ መሆን የቻሉ ብርቱ ሴት ናቸው። በእናትና በአባታቸው መኖርያ ቤት አረጋውያንን በማሰባሰብ ከሰላሳ አምስት አመት በፊት ሥራውን የጀመሩ ሲሆን እስከአሁንም ድረስ ይህው በጎ ተግባር ቀጥሎ ብዙዎችን ማቀፍ ችሏል።በአሁኑ ወቅት በአረጋውያን ማቋቋሚያና መንከባከቢያ ድርጅቱ ውስጥ ለሀገራቸው በተለያየ መስክ አገልገሎት የሰጡ አረጋውያን የሀገር ባለውለታዎች እየተደገፉ ይገኛሉ።

የ120 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ ሰውን ጨምሮ ባለፉት ዘመናት በሀገሪቱ ስልጣን ላይ የነበሩ፣ ባለሀብት የነበሩ ግለሰቦች በዚህ ድርጅት አማካኝነት ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛሉ።እንደሀገር በርካታ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሰዎች እንደዘበት ጎዳና ወድቀው ሲገኙም ይህ ድርጅት ሰብስቦ ተስፋ ሆኗቸዋል።

ይህ በጎ ተግባር ዕውቅና አግኝቶ ለማዕከሉ መስራች ለወይዘሮ አሰገደች አስፋው ከድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ሰጥቷቸዋል።

## ድርጅቱ ስለሚተዳደርበት ሁኔታ

በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ የሚተዳደረው ዘጠና ዘጠኝ በመቶ በኢትዮጵያ ህዝብ መዋጮ ነው። የመንፈሳዊ በዓላት ሲኖሩ ሰዎች ይመጡና አረጋውያንን ይመግባሉ። የመንግሥት ተቋማትም የተቻላቸውን ድጋፍ በማድረግ ይህ ድርጅት በሁለት እግሩ እንዲቆም አድርገዋል። በተጨማሪም ድርጅቱ ያሉትን የወተት ላሞች በመጠቀም ለአረጋውያን ወተት ከማቅረብ በተጨማሪ ከወተት ኪራይ ከሚገኝ ገቢ ሌሎች ወጪዎችን በመሸፈን ይተዳደራል።

በተጨማሪም ድርጅቱ ሰፊ የሆነ የእርሻ ቦታ አለው። ጊቢው ገነት በምድር የሚያስብል በአረንጓዴ ተክል ያማረ ከመሆኑ ባሻገር ቲማቲም፣ ጎመን፣ ቆስጣ፣ የቻይና ቆስጣ፣ ሰላጣ እና ሌሎች የጓሮ አትክልቶችን እንዲሁም ፍራፍሬዎች አፕል ማንጎ፣ ብርቱካን፣ ኮምጣጤ እና ሎሚን ተክለው ለገበያ ያቀርባሉ። በተጨማሪ የሸንኩርት ማሳ እና ዶሮ ከማርባት ጎን ለጎን አሳዎችም ይረባሉ። ከእነዚህ በሚገኘው ገቢ እራሱን ይደጉማል።

በእርሻ ማሳው ላይ የተለያዩ ፍራፍሬ አትክልቶችን በመትከልም ለድርጅቱ ለምግብነት ከማዋል ባለፈ ለህብረተሰቡ በመሸጥ ተጨማሪ ገቢ ያገኛል። ለወተት ከብቶች መኖ የአጨዳ ወጪን ጨምሮ በመሸፈን የኢትዮጵያ አየር ሀይልና ሌሎች ግለሰቦች በሚያደርጉት ትብብር መኖ ይሰበሰባል።ለአካባቢው ማህበረሰብም ወተት በተመጣጠኝ ዋጋ በማቅረብ ይታወቃል። በድሬዳዋ ከተማ አንድ ሊትር ወተት 110 ብር ሲሆን ይህ ድርጅት ግን በ70 ብር በማቅረብ በተጓዳኝ ለህብረተሰቡ ጥቅም በማስገኘት ላይ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ በድርጅቱ ባለቤትነት የሚተዳደር

**አካባቢውን በቅርብ የሚያውቁ ሰዎች እንደሚናገሩት አሁን ድርጅቱ ያለበት ሰፈር ከዚህ ቀደም ጫካ የነበረ ነው። ሰፈሩን በማስተካከል ለአረጋውያን ምቹ እንዲሆን ያደረጉት ወ/ሮ አሰገደች ናቸው**

ባለሶስት ወለል ህንፃን በማከራየት ገቢውን ለአረጋውያን የእለት ወጪ ያውላል።

የወ/ሮ አሰገደች ልጅ የሆነችው ወ/ሮ እመቤት እንደምትናገረው ከዚህ በፊት የነበሩ አረጋውያን ጥቂትም ቢሆን ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ይሰሩ ነበር።አረጋውያኑ ፈትል በመፍተል፤ ነጠላ በመቋጨት፣ ሸመና በመስራት ገቢ ያገኙ ነበር። አንዳንዶቹም በርበሬ በመዝራት የተሻለ ገቢ ነበራቸው። አሁን ያሉ አረጋውያን ግን እድሜያቸው የገፋና አቅመ ደካማ በመሆናቸው ምንም አይነት ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ አይሰሩም።ይህም በድርጅቱ ላይ ጫና ማሳዳሩን ትገልጻለች።

ማዕከሉ አሁንም ለአረጋውያኑ የምግብ ማብሰያ የሚጠቀመው በእንጨት ነው። በቀጣይ በሰዎች እና በከብት እዳሪ በባዮጋዝ ለመጠቀም፤ አምፖልም ቢሆን በሶላር የሚሠሩትን ለመገልገል አቅደዋል።

ከሁሉ የከፋው ግን የአረጋውያኑ መጸዳጃ ቤትና መኝታ ክፍል ሁኔታ ነው።በርካታ አረጋውያን የሚጠቀሙት በአንድ መጸዳጃ ቤት ነው።ይህ ከእድሜያቸው መግፋትና ከጤንነት አንጻር ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህም በቀጣይ እያንዳንዱ የአረጋውያን ክፍል ከኋላ ዘመናዊ ሽንት ቤት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ስግማሽ ክፍስ ...

ከገጽ 6 የዞረ

እንዲኖራቸው ማቀዳቸውን ትናገራለች።

መኝታ ቤትን በተመለከተ አረጋውያኑ በአንድ ክፍል አራት ሆነው ተጨናንቀው የሚኖሩበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህ ተሻሽሎ እያንዳንዱ አረጋዊ ለየብቻ ምቹ በሆነ መልኩ የመጨረሻ ሕይወታቸውን እንዲያሳልፉ እንደሚፈልጉም ይናገራሉ።

በማዕከሉ የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት ባላቸው ተነሳሽነት ጫማ ጠርገው እና በተለያየ መንገድ ገንዘብ ሰብስበው በጊቢው አገልግሎት የሚሰጥ ክሊኒክ ተቋቁሟል። በጎ ፈቃደኛ ሓኪሞችም ክሊኒኩ ድረስ በመሔድ የሚያክሙላቸው መሆኑን ይናገራሉ።

## ድርጅቱ በእስከዛሬው ጉዞ ምን ያህል ሰዎች ረድቷል?

የወ/ሮ አሰገደች ልጅ የሆነችው ወይዘሮ እመቤት እንደምትናገረው አሰገደች የአረጋውያን ማቋቋሚያና መንከባከቢያ ድርጅት ከመቋቋሙ በፊትም ሆነ በኋላ በርካታ ሰዎችን ሲደግፍ ቆይቷል።ሆኖም ትክክለኛውን አሃዝ አስረግጦ መናገር ባይቻልም ከቀድሞ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጀምሮ ባለሀብቶች እንዲሁም የውጭ ሀገር ዜጎች ድረስ በዚህ ድርጅት አማካኝነት ድጋፍ አግኝተዋል።

እንደ ወይዘሮ እመቤት ገለፃ፤ አሁን በግቢ ውስጥ በቁጥር ዘጠና የሚደርሱ ሰዎች አሉ፤ ከዚህ ውስጥ 20 የሚሆኑት የድርጅቱ ሰራተኞች ናቸው። በድርጅቱ ድጋፍ የሚደረግላቸው ደግሞ 70 አረጋውያን ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ እየተመላለሱ ቁርስ ምሳ እራት የሚያገኙ አሉ። በራሳቸው መኖሪያ ቤትም እየኖሩ በድርጅቱ ድጋፍ የሚደረግላቸው 20 አረጋውያንም አሉ።

## ድርጅቱ አሁን ያለበት ሁኔታ

አሰገደች የአረጋውያን ማቋቋሚያና መንከባከቢያ ድርጅት አሁንም ለበርካቶች መድህን ሆኖ የቀጠለ ቢሆንም ዋናዋ መስራች የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች በእድሜ መግፋት ድርጅቱን እንደቀድሞው መምራት ስላልቻሉ በእሳቸው ምትክ ልጃቸውን ተክተዋል።

ልጃቸው ወ/ሮ እመቤት ኑሯቸውን በካናዳ ሀገር ያደረጉ ቢሆንም በእረፍት እናታቸውን ለመጠየቅ ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ወቅት በሚያዩት በጎነት የተነሳ የበጎነት ሥራውን እንደቀጠሉ ይናገራሉ።

‹‹እናታችን እያስተማረች ያሳደገችን ቅንነትን ነው›› የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ ‹‹እኔም ይህንኑ ተከትዩ በእናቴ መንገድ ህዝቤን ለማገልገል እየሞከርኩ ነው›› ሲሉ ነግረውናል።

ወ/ሮ እመቤት እንደሚሉትም‹‹ህይወት ማለት አንድ እጅህን ለሌላ ሰው መዘርጋት ነው። የህይወትን ጣዕም ማወቅ የሚቻለው ያኔ ነው። አለበለዚያ መኖር ትርጉም የለውም። ሰው ሁልጊዜ ይህንን አደርጋለሁ፤ እንዲህ እሆናለሁ ይላል እንጂ መቼ እንደሚሞት አያውቅም፤ ሰውን በገንዘብ ብቻ አይደለም መርዳት የሚቻለው ፤ጊዜ መስጠት በራሱ ትልቅ እርዳታ ነው›› ይላሉ።

ሰው ከራሱ በላይ ያለውን እንጂ የበታቹን አያይም የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ሁልጊዜ የራስን ስሜት እየተከተሉ መኖር እርካታ እንደማይሰጥ ይናገራሉ።ከእናታቸውም የተማሩት ከራስ ይልቅ ለሰው መኖር መሆኑን ያስረዳሉ።

በመኖር ውስጥ የሚገኘው ትልቁ ስኬት ለሌሎች መድረስ መቻል ነው ይላሉ። አንድን ሰው በህመሙ ግዜ ሳንጠይቀው በሞተ ግዜ የገንዘብ መዋጮ ብናደርግ ትርጉም እንደሌለው ይናገራሉ።

## ሰዎች ምን ይላሉ

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሠሩ የነበሩት ታችዘሩ አበበ የኦዲት ሥራ ላይ ሲሰሩ ወይዘሮ አሰገደችን እንደተዋወቋቸው ይናገራሉ። በ2000 ዓ.ም አካባቢ ወደ ማዕከሉ ገብተው ሥራ የጀመሩ ሲሆን፤ ከ15 ዓመት በላይ መቆየታቸውን ያብራራሉ።

በዛ ጊዜ ወይዘሮ ታችዘሩ ወይዘሮ አሰገደችን በድሬዳዋ ሀሩር ፀሃይ በእግራቸው እየሔዱ በየቢሮ ገንዘብ ሲሠበስቡ ተመልክተው፤ ‹‹ 25 ሳንቲም ከፍለሽ ለምን በታክሲ አትሔጂም? ›› ብለው ወይዘሮ አሰገደች ሲጠይቁ፤ ‹‹ሳንቲሙ ለሁለት አረጋዊ ዳቦ ይገዛልኛል›› ብለው መልስ እንደሰጧቸው ያስታውሳሉ።

> **ሰፊ የሆነ የእርሻ ቦታ አለው። ጊቢው ገነት በምድር የሚያስብል በአረንጓዴ ተክል ያማረ ከመሆኑ ባሻገር ቲማቲም፣ ጎመን፣ ቆስጣ፣ የቻይና ቆስጣ፣ ሰላጣ እና ሌሎች የጓሮ አትክልቶችን እንዲሁም ፍራፍሬዎች አፕል ማንጎ፣ ብርቱካን፣ ኮምጣጤ እና ሎሚን ተክለው ለገበያ ያቀርባሉ**

‹‹የወይዘሮ አሰገደች ቤተሰቦች ከ30 ዓመት በላይ ካናዳ ኖረዋል። ነገር ግን ያንን ትተው መጥተው፤ ሰዎችን እያገለገሉ ነው።›› የሚሉት ወይዘሮ ታችዘሩ፤ ሰዎች ለራሳቸው ቤተሰብ እንኳን ጥያቄ ምላሽ መስጠት እና መታዘዝ ሲሰለቻቸው እነወይዘሮ አሰገደች እና ቤተሰቦቻቸው ብዙዎችን መርዳታቸው እና ለብዙዎች ጥያቄ መልስ መስጠታቸው እጅግ እንደሚያስገርማቸው ይናገራሉ።

እንደወይዘሮ ታችዘር ገለፃ፤ ወይዘሮ አሰገደች ግን ሰው ሲታመም ሃኪም ቤት ይዘው ይሔዳሉ። ከብት ሲታመም ያሳክማሉ፤ ግብርናው ሲበላሽ ወደ እዛም ይሔዳሉ። ምንም እረፍት የላቸውም።

በማዕከሉ የሚያዩትን አሳዛኝ ነገር ሲገልፁ፤ ‹‹ ለአረጋውያኑ መርጃ የተጀመረው ህንፃ ከቆመ 15 ዓመት አልፎታል። ያም ቢሆን በከፊል ለንግድ ተከራይቷል፤ ገቢው ለአረጋውያኑ እርዳታ ይደረግበታል። ነገር ግን አጠናቆ የተሻላ ገቢ ማግኘት አልተቻለም። ሰሞኑን በመከላከያ ድጋፍ እየተሠራ ነው። ነገር ግን የድሬዳዋ ሕዝብም ሆነ መንግስት አግዞ ህንፃው ቢጠናቀቅ ለማዕከሉ ትልቅ አቅም።›› ይሆናል ይላሉ።

## በማእከሉ ሰላሳ አመታት ያገለገለችው ሴት

ወይዘሮ መቅደስ ታደሰ ትባላለች። ባለ ትዳርና የልጆች እናት የሆነችው ይህች ሴት ከወይዘሮ አሰገደች ጋር የተገናኙበትን አጋጣሚ በዚህ መልኩ ትናገራለች። “ ድሬዳዋ ውስጥ እናቴን ወ/ሮ አሰገደችን ሳቃት ከሰላሳ አመት በላይ ሆነኝ። እናቴ የምላት ወልዳኝ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ እናት አድርጌ ስለማያት ነው ።

እኔም በተፈጥሮዬ ድሃ እወድ ስለነበር ከሷ ጋር አንድ አይነት የነፍስ ጥሪ ስላለን ተገናኝተናል። በአንድ ወቅት ታዲያ እናቴ ወይዘሮ አሰገደች ድል ጮራ ሆስፒታል አካባቢ የወደቁ አረጋዊት ለማንሳት ሲሞክሩ ከእኔ ጋር ተገናኘን።በጊዜው አግዣት ወደ ቤቷ በወሰድኩበት አጋጣሚ ነበር የተገናኘነው። ከዛ በኋላ ነው አንግዲህ እናቴን ተከትዬ መጣሁ ። አብሪያት ከሆንኩም ከሀያ አመት በላይ ሆኖኛል።

መጀመሪያ ድሆችን በቤቷ ነበር የምትሰበስበው ፤ከዛ በኋላ ጫካ በመመንጠር የአረጋዊያን መሰብሰቢያ ተቋም እንዲቋቋም ያደረገች ብርቱ ሴት ናት። እናቴ በጣም ደከመኝ ሰለቸኝ የማታውቅ ሰው ናት። ለራሷ ምቾት የማትጨነቅ፤ የማይርባት፤ የማይደክማት ሴት ናት። የምትተኛው እንኳን ኬሻ ላይ ነበር ።

ለአረጋውያን የሚቀርበው ምግብ የሚዘጋጀው በጥንቃቄ ነው።የሚቀርበው ምግብ ሁሉ የሚዘጋጀው ቤት ውስጥ ነው። አረጋዊያኑ የሚበሉት ምግብ ጣእሙ እንዳይቀያየር እንኳን ከፍ ያለ ጥንቃቄ ታደርጋለች።

እናቴ በጣም የእምነት ሰው ናት ።አንዴ ታማ ቤቱን እያስተዳደርኩ አያለ ጤፍ ያልቃል። ወዲያው እናቴ ጋር ገብቼ ለሁለት ጊዜ ቡኮ የሚሆን ነው የቀረው ስላት እኔ ምን አግብቶኝ ነው፤ የሰማይ አምላክ እራሱ አረጋዊያኑን ይመግባቸዋል አለችኝ። ይህን ባለች ቅፅበት ውስጥ አንድ ድርጅት ሁለት መቶ ኪሎ ነጭ ጤፍ ላከለን። በእምነት በረከትን የምታገኝ ታላቅ ሰው ናት። ከእሷ በእምነት መፅናትን ተምሪያለሁ “ ትላለች።

የድሬደዋ ሰው መስጠት የሚችለው ነገር እንኳን ቢያጣ መጥቶ የአረጋውያን ገላ ያጥባል፤ጸጉራቸውን ይቆርጣል፤ይላጫል።የታይዋን ሰዎች በአል ጠብቀው አዳዲስ ልብስ አረጋዊያኑን ያለብሳሉ። ሰርግ ልደት አና ዝክር በጊቢው ስለሚከበር አንድም ቀን ጎድሎ እንደማያውቅ ወይዘሮ መቅደስ ትናገራለች።።

ወይዘሮ መቅደስ አክላም ቤቱ በርካታ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የሚመረትበት፤ ላም ረብቶ ወተት ከግቢው ነዋሪዎች ፍጆታ የተረፈውነ በመሸጥ ጎዶሎ የመሙላት ስራ ይሰራል።

ወይዘሮ አሰገደች ለአረጋዊያኑ ፍጆታ የሚውል ነገር ለመለመን ስትሄድ ቁጭ በይ እንኳን ሲሏት “የኔ ቢጤ ቆሞ ነው የሚለምነው ፤ሲደረግለት ነው ቁጭ የሚለው” በማለት ተማፅና በግቢዋ ያስጠለለቻቸውን አረጋዊያን ትመግባለች።

መቀመጥ እርጅናን ያብሳል የምትለው ወይዘሮ አሰገደች አቅም የላቸው አረጋዊያን በሚችሉት ሁሉ የገቢውን ስራ እንዲረዱ ያደርጉ ነበር።አረጋውያን በሞት እስኪለዩ ድረስ መጦርያ ቤታቸውነ ወደውት እንደ ቤተሰብ እንደሚኖሩ ብዙዎች ይናገራሉ።

## በማእከሉ የሚገኙ አረጋዊያን ምስክርነት

በአረጋዊያን ማእከሉ የሚኖሩት ወይዘሮ አፀደ ተሰማ የተወለዱት ወሎ እንደሆነ ይናገራሉ። ከወሎ ወደ ድሬደዋ የመጡት ከባላቸው ጋር ሲሆን ልጅ ባለመውለዳቸው ምክንያት ከባላቸው ጋር ተለያይተው ሳብያን የተባለ አካባቢ ይኖሩ እንደ ነበር ይናገራሉ። አቅመ ደካማ ጧሪ ሲያጡ ግን ወደ አረጋዊያን ማእከሉ የመጡት እኚህ ሴት በማእከሉ ሶስት አመታትን አሳልፈዋል።

ልጅ ባለመውለዳቸው ምክንያት ሲከፉ የነበሩት እማማ አፀደ የወንድማቸውን ልጅ በሶስት አመቷ አምጥተው ያሳደጉና ያስተማሩ ሲሆን ያላቸውን ንብረትና ጌጥ ሸጠው ቤታቸውንም ጭምር ከሞቱ በኋላ እንደትወርስ ይሰጧታል። ልጅቷ ባል ሰታገባ ቤት ንብረታቸው አንዴ በስሟ ሰለሆነ እማማ አፀደን አውጥታ ጎዳና በመጣል ቤቱን ሸጣ አዲስ አበባ ገባች።

ጎዳና መውጣታቸውን የተመለከተች አንዲት የጎረቤት ልጅ ይዛቸው ብትቆይም እሷ አሜሪካ ሀገር በመሄዷ የተነሳ ወ/ሮ አሰገደች ወደ አቋቋሙት ማእከል እንደመጡ ይናገራሉ። በተቋሙ መንፈሳዊ ህይወታቸውን እያካሄዱ በልጆች እንደሚደረግላቸው አይነት አንክብካቤ እየተደረገላቸው በመኖር ላይ እንደሚገኙ ያስረዳሉ።

ሌላዋ በደርጅቱ የሚኖሩ አረጋዊት ወይዘሮ አለሚቱ መኮንን ይባላሉ። እማማ አለሚቱ ወሎ ስጎን የተባለ ቦታ የተወለዱ ሲሆን አግብተው የወለዱና አንድ ልጃቸው የሞቱባቸው ሲሆን ወደ ድሬደዋ ሰው ተከትለው መጥተው ለመሰራት እየሞከሩ ነበር። በጦርነት በፈንጂ አግራቸውን ያጡት በዚሁ ምክንያት ወደ ተቋሙ መጥተው የሚረዱ እናት ናቸው።

እግር አልባዋ እናት በደርግ ጦርነት ወቅት የአካል ጉዳት የገጠማቸው ሲሆን እርጅና መጥቶ ሳይጫናቸው በፊት የአረጋዊያን ማእከል ውስጥ ተቀምጠው መስራት የሚችሉትን ስራ በሙሉ ይሰሩ እንደ ነበረ ያስታውሳሉ።

ከሰላሳ አምስት አመት በላይ በማእከሉ የቆዩት እናት ምሰር መልቀም ፤ሽንኩርት መላጥ የመሳሰሉ ስራዎችን ይሰሩ እንደ ነበር ያስታወሳሉ። በማእከሉ ምንም ሳይጎልባቸው ፤ ፅዳታቸው ተጠብቆ፤ በልተው፤ ጠጥተው፤ የእርጅና ዘመናቸውን መቆየታቸው ወይዘሮ አሰገደችን እያመሰገኑ እንዲኖሩ አንዳደረጋቸው ይናገራሉ።

ሌላው በአረጋዊያን ማእከል የሚኖሩ አባት አቶ ገዛሄኝ ሄርፖ ይባላሉ። አቶ ገዛሄኝ የተወለዱት ሂርና ሲሆን እስከ ስምንተኛ ክፍል በተወለዱበት አካባቢ ተምረዋል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአሰበ ተፈሪ መማራቸውን ያስታውሳሉ።

በወቅቱ በነበረው የእርስ በእርስ ግጭት የተነሳ ትምህርታቸውን አቁመው ወደ ጦርነት ከገቡት ዘጠኝ ጓደኞቻቸው መካከል አሳቸው ሲተርፉ ወደ ግብርና ስራ መሰማራታቸውን ይናገራሉ። ከአስረኛ ክፍል አቋርጠው እርሻ የገቡት አባት ስራቸውን እየሰሩ የተወሰነ ጥሪት እያፈሩ ከቆዩ በኋላ በዱር በገደሉ ያለህ ወገን ሰራዊቱን ተቀላቀል ሲባል የእናት ሀገር ጥሪን ተቀብለው ወደ ውትድርና መግባታቸውን ይናገራሉ።

ድሬደዋ በ1972 የመጡት እኚህ ሰው በጥበቃም በጉልበትም ሰራ ሲሰሩ ቆዩ ። ለአመታት ያገኙትን እየሰሩ የሰው እጅ ሳይጠብቁ ቢኖሩም በቅርብ ጊዜ ቤታቸው በጎርፍ በመወሰዱ የተነሳ ተረጂ ሆነው ወደ ማእከሉ መምጣታቸውን ይናገራሉ።

በተቋሙ መግባታቸው ቡናው ጫወታው ደስ የሚል እረፍት እንደሰጣቸው ይናገራሉ። ሰው እንደ ቤተሰብ ስለሚጠየቅ ይደሰታሉ። ንፁህ አልባሳትን በማግኘታቸው ደስታ እንደተሰማቸው ይናገራሉ።ለዚህ ሁሉ መሰረት የሆኑትን ወይዘሮ አሰገደች አስፋውን ያመሰግናሉ፤ረጅም ዕድሜም ይመኛሉ።

# ሳምንቱን በታሪክ

# አብዮተኛው ግንቦት 20

ዋለልኝ አየለ

ከስድስት ዓመታት በፊት ግንቦት 20 ዜና ነበር፤ እነሆ አሁን ታሪክ ሆኗል። ከስድስት ዓመታት በፊት ድል ባለ የካድሬ ድግስ በድምቀት ይከበር ነበር። እነሆ ዘንድሮ ግን በዋዜማው «ነገ ሥራ ይዘጋል አይዘጋም?» አወዛጋቢ ሆኖ ነበር። ምንም እንኳን በአዋጅ ያልጸደቀ ቢሆንም በቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ላይ ስለተመዘገበ ዝግ ሆኖ ውሏል። ወደፊት የሚኖረውን ዕጣ ፋንታ ወደፊት እናያለን።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን አብዮተኛውን ግንቦት 20 በዝርዝር እናያለን። ከዚያ በፊት ግን ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን አጠር አጠር አድርገን እናስታውስ።

ከ119 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 19 ቀን 1897 ዓ.ም ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ተወለዱ። ከዚህ በፊት ሙሉ ታሪካቸውን በዝርዝር ያስነበብን ቢሆንም አሁንም በጥቂቱ እናስታውሳቸው። ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ደቡሳ ከአዲስ አበባ 104 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ወሊሶ ማሩ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ተወለዱ። በትምህርት ረገድ ፊደልን በአካባቢያቸው የቆጠሩ ሲሆን፣ የሃይማኖት ትምህርትም ተምረው በዲቁና ቤተ ክርስቲያንን እስከማገልገል ደርሰዋል።

ከ1912 ዓ.ም እስከ 1918 ዓ.ም በቀድሞው የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ሀብተዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) አስተዳደር ውስጥ ወታደራዊ ተግባራትን ተወጥተዋል። ከ1919 ዓ.ም እስከ 1924 ዓ.ም በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ቤተ መንግሥት ውስጥ በጋሻ ጃግሬ ደንብ አገልግሎታቸውን አበርክተዋል። ከ1921 ዓ.ም እስከ 1928 ዓ.ም ወደ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋው ወሰን ተዛውረው በማገልገል የባላምባራስነት ማዕረግ አግኝተዋል። በ1928 ዓ.ም በነበረው የማይጨው ጦርነት ከጣሊያን ጋር ተዋግተው ተንቤን ላይ ከፍ ያላ ጀብዱ ሠርተዋል። ከ1929 ዓ.ም እስከ 1933 ዓ.ም የብዙ ሺህ አርበኞች መሪ ሆነው በየአውራጃው በመዞር ለ5 ዓመታት ከፋሺስት ጣሊያን ጋር ተዋግተዋል።

ገረሱ ዱኪ በየአወራጃው በመዞር የጣሊንን ከከፋፍለህ ግዛ የውጭ ፖሊሲ በፅኑ ተቃውመዋል፤ ገረሱ የጣሊያንን ሴራ ገርስሰዋል። ወታደራዊ ስትራቴጂስት እና ጀግና በመሆናቸውም ከቀዳማዊ ኃይለሥለሴ እጅ ቤልጅየም ሰራሽ ቤልጂግ ጠመንጃ ተሸልመዋል።

ከ83 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 19 ቀን 1933 ዓ.ም የደርግ ሊቀመንበር እና የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ተወለዱ። ግንቦት የደርግ እና የኢህአዴግ ታሪክ እስከሚመስል ድረስ፤ መሪዎቹ የተወለዱት በግንቦት ወር፣ የሚመሩት ድርጅት የታቀደውና የተወለደው በግንቦት ወር፣ ተቃዋሚዎቻቸው የጠነከሩባቸው በግንቦት ወር ሆኗል። ከ83 ዓመታት በፊት የተወለዱት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፤ በጋዜጠኛና ደራሲ ገነት አየለ አማካኝነት ባለፈው ሰኞ ግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም 83ኛ ዓመታቸውን ሲያከብሩ ከባለቤታቸው ወይዘሮ ውብአንቺ ቢሻው ጋር የተነሱት ፎቶ በማህበራዊ ገጾች ሲዘዋወር ውሏል።

ከ25 ዓመታት በፊት ግንቦት 19 ቀን 1991 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሞባይል ስልክ አገልግሎት ተጀመረ። በዓለም የሞባይል ስልክ ታሪክን ስንመለከት እንደ መጀመሪያ የሚቆጠረው በ1965 ዓ.ም (እ.አ.አ 1973) «ሞቶሮላ» የሚባለው በቅርጹ ፖሊሶች የሚይዙትን መገናኛ የመሰለ፣ በመጠኑ ግን የአነስተኛ ሬዲዮ መጠን ያለው ነበር። የሞባይል ስልክ በኢትዮጵያ አገልግሎት ሲጀምር መጠኑና ቅርጹ በመጠኑም ቢሆን ዝግመተ ለውጥ ያሳየበት ነበር።

ከ1491 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 20 ቀን 525 ዓ.ም በገናናነታቸው ከሚጠቀሱት የኢትዮጵያ ነገሥታት መካከል አንዱ የነበሩት ባሕር ተሻጋሪውና መናኙ ንጉሥ አፄ ካሌብ አረፉ። እኚህ የአክሱም ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ንጉሥ የዛሬዋን ሀገረ ኤርትራን ጨምረው ቀይ ባህርን የሚያስተዳድሩ ንጉሥ ነበሩ። የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ይህን ለማስታውስ ለመጀመሪያ ልጃቸው «ካሌብ» የሚል ስም እንዳወጡለት በመጽሐፋቸው ገልጸዋል።

ከ10 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም ዝነኛው ጀርመናዊ የፊልም ተዋናይና በጎ አድራጊ ካርልሄይንዝ በም አረፉ። ካርል «የሰዎች ለሰዎች ድርጅት (Menschen für Menschen)» የተሰኘውን የበጎ አድራጎት ድርጅት በማቋቋም በርካታ ኢትዮጵያውያንን ከችግር ታድገዋል፤ ትምህርት ቤቶችንና

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር (ኢህአዴግ)

ጤና ጣቢያዎችን ገንብተዋል። ለበጎ አድራጎት ስራቸውም የክብር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ተሰጥቷቸዋል። በአንዳንድ ከተሞችም ሀውልት ቆሞላቸዋል።

ከ110 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 23 ቀን 1906 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ አባታቸውን ራስ ሚካኤልን «ንጉሰ ወሎ ወትግሬ» ብለው አነገሱ።

አሁን ወደ አብዮተኛው ግንቦት 20 ታሪክ እንሂድ። ግንቦት 20 አብዮተኛ የታሪክ ክስተት ነው። ቀኑን በድምቀት ያከብረው የነበረውና የታሪኩ ባለቤት ነኝ የሚለው ኢህአዴግ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ርዕዮተ ዓለሜ ነው ይል ነበር። ወዲህ ደግሞ ግንቦት 20ን አብዮተኛ የሚያደርገው አዲስ የአገር አወቃቀር ቅርጽ ያስያዘ ስለሆነ አዲስ አብዮት ተፈጥሯል ማለት ነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል የኢትዮጵያ ካርታ አዲስ ቅርጽ ያዘ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከመሃሉ ላይ ኮከብ ስለተጨመረበት አዲስ ቅርጽ ያዘ። ክልሎች የየራሳቸው ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ስለፈጠሩ አዲስ አብዮት ተፈጠረ። በእነዚህና ሌሎች ነገሮች ግንቦት 20 ልክ እንደ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም አብዮተኛው የታሪክ ክስተት ሊባል ይችላል።

ከ33 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ኢህአዴግ ወታደራዊውን የደርግ መንግሥት ገርስሶ አዲስ አበባን ተቆጣጠረ። የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር የነበሩ የጻፏቸው መጻሕፍት፣ በተለያዩ መድረኮች የተናገሯቸው ንግግሮች፣ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የተሰሩ ዘጋቢ ፊልሞች... እንደሚያሳዩት ኢህአዴግ ደርግን ያስወገደው በሕዝብ ትብብር ነው።

ምንም እንኳን ጦርነቱ የዓመታት ቢሆንም ኢህአዴግ ግንቦት ሃያን በተለየ ያከብረው የነበረው አዲስ አበባን የተቆጣጠረበትና ቤተ መንግሥት የገባበት ቀን ስለሆነ ነው።

የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት እንደሚያሳዩት ኢህአዴግ ደርግን ለማስወገድ ሕዝባዊ ድጋፍ የሚያስገኙ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። ከእነዚህም አንዱ የጦርነቱን ዘመቻዎች የአካባቢው ሰዎች በሚያከብሯቸውና በሚያደንቋቸው ሰዎች ይሰይም ነበር። የአካባቢው ሰዎች በሚናገሩት ቋንቋ ይሰይም ነበር።

ለምሳሌ፤ በወለጋ እና በሌሎች የምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የነበረውን ዘመቻ «ቢሊሱማ ወልቂጡማ» ብሎ ነበር የሰየመው። ቃሉ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን ነፃነትና እኩልነት ማለት እንደሆነ ሲነገር ቆይቷል። በዚህ ስም የሰየመውም የአካባቢው ሰው የኦሮምኛ ተናጋሪ ስለሆነ ነው።

በወሎ በኩል የነበረው ዘመቻ ደግሞ ዘመቻ ዋለልኝ ተብሎ ተሰይሟል። ዋለልኝ መኮንን የወሎ ተወላጅ ሲሆን የብሔር ፖለቲካ አቀንቃኝ ነበር። ኢህአዴግ ይህን የተጠቀመው ዋለልኝ መኮንን የወሎ ተወላጅ ስለሆነ ወሎዎች ይወዱታል ብሎ ሳይሆን ምናልባትም የብሔር ፖለቲካ ጀማሪና አቀንቃኝ ስለነበረለት ይሆናል።

በጎንደር በኩል የነበረው ዘመቻ ደግሞ እስከ ጎጃም ድረስ «ዘመቻ ቴዎድሮስ» ይባል ነበር። በዚያ አካባቢ ያለው ማህበረሰብ የአጼ ቴዎድሮስ ነገር ሲነሳ ወኔው ይቀሰቀሳል ብሎ ስላሰበ ይመስላል።

አራተኛውና አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት የመጨረሻው ዘመቻ ደግሞ «ዘመቻ ወጋገን» ይባላል። «የመጨረሻዋ ጥይት የተተኮሰችበት» ይሉታል የኢህአዴግ ሰዎች። በእርግጥ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ከቤተ መንግሥቱ ዙሪያ በስተቀር መሃል ከተማ ውስጥ የውጊያ ተኩስ እንዳልነበር በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ጽፈዋል። ለዚህ ክስተት አለመኖር የደርጉ መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከሳምንት በፊት (ግንቦት 13 ቀን) አገር ለቀው መሄዳቸው አስተዋፅዖ ሳይኖረው አይቀርም።

በ2008 ዓ.ም ግንቦት 20 ሲከበር የኢህአዴግ ጽሕፈት ቤት ካቀረበው ጽሑፍ፤ የግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ክስተት የሚከተለውን እናስታውስ።

«.... አዲስ አበበ በሦስት አቅጣጫ በኢህአዴግ ሰራዊት ተከባለች። ከየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የሚወጣም ሆነ የሚገባ የለም። የቀለበቱ ማጥበብ ቀጥሏል። አምቦ የነበረው ሰራዊት ወደ ሆለታና ታጠቅ ተጠጋ። በጅማ በኩል የነበረው ግልገል ግቤን ተሻግሮ ወሊሶን አልፎ ወደ አለም ገና ተጠግቷል። ደብረ ብርሃን የነበረው ሃይል ገሚሱ ወደ ደቡብ ምስራቅ በመጓዝ ደብረ ዘይትን ከበባት። ማንኛውም የጦር አውሮፕላን ወደ ሰማይ አልወጣም፤ አልወረደም።

....ግንቦት 19 ቀን 1983 ልክ ከቀኑ 10 ሰዓት ወታደራዊ ዘመቻውን በበላይነት የሚያስተባብረው ቡድን ለመጨረሻ የሰላም ውይይት ሎንደን ከነበረው የበላይ አመራር «ቀጥል» የሚል አጭር መልዕክት ደረሰው። ቀድሞ በተደረገው ጥናት አዲስ አበባ በሦስት ግንባር ተከፍላለች።

በአምቦ ግንባር የነበረው በጎጃም በር በኩል ወደ ፒያሳ በመዝለቅ መርካቶን ተቆጣጥሮ ወደ ጅማ መንገድ ያመራል።

ሁለተኛው ግንባር በደብረ ዘይት የሚመጣ በአቃቂ ገብቶ ንፋስ ስልክ፣ ጎተራ፣ ቄራ፣ አራተኛ ክፍለ ጦር፣ ስታዲየም ጨምሮ እስከ ሜክሲኮ ያለውን ይይዛል።

ሦስተኛው በሰንዳፋ የሚመጣ በኮተቤ በመውረድ ብረታ ብረት ፋብሪካ ከደረሰ በኋላ ለሦስት ንኡስ ግንባር ይከፈላል። አንዱ በመገናኛ በኩል ወደ ኤርፖርት ያመራል። ሁለተኛው ክፍል በ22 ሰንጥቆ ወደ መስቀል አደባባይ በመሄድ ታችኛውን ቤተመንግስት ይቆጣጠራል። ሦስተኛው ክፍል በእንግሊዝ ኤምባሲ አቅጣጫ በግንፍሌ አድርጎ ወደ አራት ኪሎ በመግባት ቤተ መንግሥትን ይቆጣጠራል።

ኮማንደሮቹ ይህንን ድልድል በማድረግ ሌሊቱን በሙሉ ሲዘጋጁ አደሩ። እነ ሐየሎም በነበሩበት አቅጣጫ ታጠቅ አካባቢ የነበረው ሃይል ማታ ወደ ከተማ የመፍረስ ምልክት ስለታየ ይህ ሃይል ወደ መሃል ከተማ ከገባ አላስፈላጊ ዋጋ የሚያስከፍል ውጊያ ስለሚያስከትል አስቀድሞ መያዝ አለበት ተብሎ ስለተወሰነ በዋዜማው የተወሰነ ሃይል ቀድሞ ወደ ቦታው እንዲጠጋ በማድረግ በኮልፌ 18 ማዞሪያ በኩል ተዘጋ። ከከተማው ወደ ውጪ እንዲበተንም ተደረገ።

አስቀድሞ የወጣው ስትራቴጂ በሚገባ የሰራ መሆኑ እየተረጋገጠ መጣ። የመንግሥት አብዛኛው ወታደር ከአዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት እንዲበታተን ተደረገ። ገሚሱ መሳሪያ የያዘ ገሚሱ መሳሪያ የሌለው እየተንቀረፈፈ ከሚገባ በስተቀር ተደራጅቶ ወደ ከተማዋ የሚያፈገፍግ ሰራዊት አልነበረም። ይህ ለኢህአዴግ ትልቅ ድልና ስኬት ነበር። በህዝቡ ዘንድም ስጋትን የቀነሰ ነበር።

የወጋገን ዘመቻ ዋና ዓላማው የቀረውን ሰራዊት መደምሰስ ሳይሆን ከተማዋን በብልሃት መቆጣጠር ነበር...»

ኢህአዴግ ይህን እያደረገ በለንደን ደግሞ ከደርግ መንግሥት ጋር ድርድር ነበር። የፖለቲካ ተንታኞች የለንደኑን ኮንፈረንስ «ሳይጀመር የተጠናቀቀ ድራማ» በማለት ሲገልጹት ነበር። በእርግጥም ኮንፈረንሱ የግማሽ ቀን ዕድሜ ብቻ ነው የነበረው። ዋና አደራዳሪው ሚስተር ሄርማን ኮህን ተደራዳሪዎቹን በተናጥል ማነጋገራቸው ብቻ ነው። በሚቀጥለው ቀን ግን ሚስተር ሄርማን ኮህን ረፋዱ ላይ ጋዜጣዊ ጉባኤ በመጥራት ኮንፈረንሱ መሰረዙን አስታወቁ። ኢህአዴግ በአዲስ አበባ፣ ህግሓኤ በአስመራ የየራሳቸውን መንግሥት እንደሚመሰርቱም ገለጹ።

ለኮንፈረንሱ መበተን ምክንያት የሆኑት በመጨረሻው ሰዓት የኢህዲሪ ፕሬዚዳንት በመሆን የተሰየሙት ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ናቸው። ጄኔራል ተስፋዬ ለሚመሩት መንግሥት ባለስልጣናት ሳያስታውቁ ዕለተ ሰኞ ግንቦት 19 ቀን 1983 ዓ.ም ረፋዱ ላይ ለአሜሪካ ኤምባሲ «የጦር ሰራዊቱ ከቁጥጥሬ ውጭ ሆኗል፣ በአንዳንድ አካባቢዎችም ዘረፋ ተጀምሯል» የሚል መረጃ ሰጡ፤ ለራሳቸውም የኢጣሊያ ኤምባሲ ገብተው ጥገኝነት ጠየቁ (በወቅቱ ወደ ኤምባሲው አብረዋቸው የገቡት ባለስልጣናት አቶ ሀይሉ ይመኑ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ሻምበል ብርሃኑ ባይህ የቀድሞ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር እና ሌተናል ጄኔራል ሐዲስ ተድላ የኢህዲሪ የጦር ሀይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ናቸው)።

የአሜሪካ ኤምባሲም ከጄኔራል ተስፋዬ የሰማውን መረጃ ለንደን ለሚገኙት ሚስተር ሄርማን ኮህን አስተላለፈ። በዚህም መሰረት ሚስተር ኮህን ምሽት ላይ በኮንፈረንሱ አካሄድ ላይ ለውጥ መደረጉን አስታወቁ። አዲስ አበባ እንደ ሞቃዲሾ እና እንደ ሞኖሮቪያ እንዳትሆን የኢህአዴግ ጦር ወደ ከተማዋ መግባት እንዳለበትም ተናገሩ። የኢህአዴግ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊም ጦራቸው አዲስ አበባን እንዲቆጣጠር ትዕዛዝ ሰጡ። በመሆኑም የኢህአዴግ ጦር ከሌሊቱ 8፡00 ጀምሮ ወደ አዲስ አበባ መግባት ጀመረ። ያንን ኦፐሬሽን የመሩት አዝማቾች ጄኔራል ጻድቃን ገብረትንሳኤ፣ ጄኔራል ሐየሎም አርአያ፣ ጄኔራል አበበ ተክለ ሀይማኖትና ጄኔራል ሳሞራ የኑስ እንደሆኑ ይነገራል።

ማክሰኞ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ከጧቱ 1፡00 ሰዓት አንድ የኢህአዴግ ታጋይ ከኢትዮጵያ ድምጽ ብሔራዊ አገልግሎት (የኢትዮጵያ ሬዲዮ) እንዲህ ሲል ተሰማ።

«የዘመናት የህዝብ ብሶት የወለደው ጀግናው የኢህአዴግ ሰራዊት ደርግ ሲጠቀምበት የነበረውን የአዲስ አበባ ሬድዮ ጣቢያ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል፤ ግንቦት 20 ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሦስት ዓመተ ምህረት»

በሕወሓት ጀማሪነትና መሪነት የተደረገው የትጥቅ ትግል በዚህ መልኩ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ለ27 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን መራ። በ2010 ዓ.ም ለውጥ መጣ፤ ከዚያ በኋላ ያለው ታሪክ ሳይሆን ዜና ነው። እነሆ ግንቦት 20 ግን ታሪክ ሆነ!

ስፖርት እና መዝናኛ

## የዝነኞች ገጽ

# የአባቱ ልጅ ባለ ዜማ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

"የአባት እዳ ለልጅ" ብለው ይላሉ አበው። ምን ነካቸው ባንልም ለዛሬው ግን ተረቱ እራሱ ተረት ሊሆን ነው። ይህን አባባል የሚያለዝቡ አባትና ልጆች ከወዲህ ግድም ሳይገኙ አልቀረም። ባይሆን ለዛሬው "ወንድ ልጅ ተወልዶ፤ ካልሆነ እንዳባቱ..." የሚለው የሚያስማማን ይመስላል። አይረሴው ሙዚቀኛ ተፈራ ካሳ የሙዚቃ ፈርጥ ለመሆን የቻሉ ሁለት ወንድ ልጆቹን አስከትሏል። አባት ዜመኛ፤ ልጅ ሙዚቀኛ፤ ወንድምም ዜመኛ...የድምጻዊ ልጅ ድምጻዊ ... ከቤቱ ውስጥ ለልጅ የሚተርፈው የአባት እዳ ሳይሆን በረከት ነው። በአባት በረከት ልጅ እያስቀደሰ ወንድም ይሰልስበታል። የሙዚቃ ጥበብ እንደ ውርስ በተዋረድ እየተምዘገዘገ ከአባት ለልጅ በረከት ሲዘንብ፤ ያውም ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ የጥበብ በረከት ከመቶ መታደል ውስጥ የሚገኝ አንድ እድል ነው። የወይኖቹ ዘለላዎች ቢበረከቱም ለዛሬው አንዱን ጣፋጭ ዘንጋዳ ለመምረጥ የግድ ይለናል።በእንኮይ አቁማዳ እጣ ማውጣቱም ሳያስፈልገን የአይን እርግብግቢት ቅንድባችን ይመራናል።አባትን በላቀውና በሌላኛው የነገ ተስፋ አንጋፋውን የበኩር እንከተል። ግርማ ተፈራን ለማለት ነው።መቼስ የዚህን ጊዜ "ታድያለሁ በቃ" የምትለዋን ዜማ ያዜምልን ይሆናል። ለዛሬው ምርጫችን እንድናደርገው የገፋፋን አንድ ጉዳይ ስለመኖሩ ግን ከወዲሁ ጠቆም አድርገነው እንለፍ። ይኼውም የ2016ቱ የ"ለዛ አዋርድ" ነበር። ከቀናት በፊት 13ኛው የ"ለዛ አዋርድ" የሽልማት ሥነ ሥርዓት ስለመካሄዱ እንግዳ የምንሆን አይመስለኝም።ከነበሩት በርካታ የሽልማት ዘርፎች አንደኛው "የአመቱ ምርጥ አልበም" የሚል ነበር።ታዲያ ማን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት እሩቅ አይመስለኝም።ግርማ ተፈራ ካሳ እርሱ እራሱ ሆኖ ታይቷል። ከዳዊት ይፍሩ እጅ በክብር ሽልማቱን ተቀብሏል፡፡

ደግሞ በሶምሶማው አንደኛው ሰፈር ደረስ መለስ አድርጎ ይመልሰን። ከእዚህ አዲስ አበባ፤ በአራት ኪሎ ስድስት ኪሎ አሳብረን ፈረንሳይ ሌጋሲዮን ስንገባ ከወዴት ይሆን ግርማ ማለት አይቀርም። እዚያ ሠፈር እንደሆነ ፍሬው ቀርቶ እንክርዳዱን ቢዘሩት እንኳን ደርሶ አዝመራ ነው። ቄሱ ይሁኑ ሼሁ ማናቸው እንደባረኩት ባይታወቅም የመንደሩ የጥበብ አውድማ በጋ ክረምቱን አሽቶና አብቦ ጎተራውን እየሞላ ይፈሳል። ይህም ሀቅ ነው። ሠዓሊ ሙዚቀኛው፤ ጸሀፊ ጋዜጠኛው፤ ተዋናይና ስፖርተኛው ሁሉ ያለውን ጥበብ አንጠልጥሎ እየገባ ይሁን ከገባ ወዲህ...ብቻ ግን የኢትዮጵያን የኪነ ጥበብ ነጠላና ጋቢ የደረቡ ስመጥር ሁሉ ከወዴት ይሆኑ? ሲባል አንድና አንድ መገኛቸው ፈረንሳይ ሌጋሲዮን የሚል ነው።እዚያ ሠፈር ውስጥ ተወልዶ አድጎ፤ አሁንም ከዚያው የከተመው ግርማ ተፈራ ምናልባትም ሚስጥሩን ከማናችንም ደህና አድርጎ ያውቀው ይሆናል።ይህ ብቻም ሳይሆን በጥላሁን ገሠሠና በማህሙድ አህመድ እየተቆነጠጠ ያደገ ሰው በመሆኑ እድል ከነጅራቷ ዞራለታለች። እኚህን ሁለት ብርቱ ሙዚቀኞችን ሲወዳቸው መውደዱ መጠን የለውም። ስማቸውን ጠርቶም አይጠግበውም። ከፈረንሳይ የተተከሉት ሁለቱ የሙዚቃ ምሰሶዎች የተፈራ ካሳ የአባቱ ጓደኞች ነበሩ። ሙዚቃ ሲያጠኑ እንኳን አንድ ላይ ነውና የመገናኛ ታዛቸው በብዛትም ከነ ግርማ ቤት ውስጥ ነበር። ከፊትና ኋላ ከወደ አፍና አፍንጫ በተሰካካው የመኖሪያ ቤታቸው ቡናውን ተጠራርተው፤ ጸበል ጻድቁን ተቃምሰው በእድር ማህበሩ አብረው ተገኝተዋል። የአንዱ ልጅ ለሌላው ሲላላክ ሲያጠፋ ተኮርኩሞ ሲያለማ ተወድሶና ተሸልሞ አድጓል። እንግዲህ በዚህ ውስጥ ያደገው ግርማ ተፈራ ምን ዓይነቱ ልጅ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ እዳው ገብስ ነው፡፡

በኛ ሀገር ውስጥ በተለይ ደግሞ በቀደመው ዘመን ውስጥ ሙዚቀኛ ለመባል ካለሙት ለመድረስ ፈተናው ይህ ነው የሚባል አልነበረም። ልጆቻቸው አዝማሪና ዘፋኝ እንዳይባሉ አንካሴያቸውን ጨብጠው የሚቆሙ ወላጆችም ብዙ ነበሩ። ይህን ሳስብ ታዲያ፤ የሙዚቀኛው ልጅ ግርማ ተፈራስ ይህቺን ቦታ እንደምን ተሻገራት? ተቃውሞ ገጠመው ወይንስ በአባቱ ድጋፍ ሰተት ብሎ ወደ ሙዚቃው ገባ? ብዬ ባሰላስልም እራሱኑ የመጠየቁን እድል አላገኘሁምና ከዚህ ቀደም ካደረጋቸው ቃለመጠይቆቹ ውስጥ ምላሹን ለመቃረም ሞከርኩ። የሙዚቀኛ ልጅ ነውና ያለጥርጥር ተቃውሞ አይኖረውም ብላችሁ ታስቡ ይሆናል፤ ነገር ግን እንደዚያ አልነበረም። ልጁ የእርሱን የእግር ዳና ተከትሎ ሙዚቀኛ እንዲሆን አባት ፍላጎትም ሆነ ምኞት አልነበረውም። የሚያስገርም ቢመስልም ያለ እናት ላሳደገ ሙዚቀኛ አባት ግን በተራ ምክንያት የሆነ አይደለም። እርሱም በእርግጠኝነት ባያውቀውም ሊሆን የሚችለው ምክንያት ግን ከሙያው ፍቅር ጋር መሳ ለመሳ የቆመውን የመገፋትን የመከራ ገፈት እንዳይቀምስ ነበር። አባት በሙዚቃ ገመድ እያለፈበት ባለው በዚህ ከመንደር እስከ ሀገር በተቆለለው ድካምና እንግልት በበዛበት ተራራ እንዲንገላታ ካለመፈለግ የመጣ ነበር። ለውሳኔውም የቤተሰብ ሸንጎ ከጠረጴዛው ዙሪያ ተሰይሞ መከረበት። የመጨረሻውን የግርማን የሀሞቱን ልክና የፈነቀለውን ወኔ ሲመለከት አባት ውሳኔውን መቀየሩ አልቀረም። እንግዲያውስ አለ አባት፤ እንደኔ በልምድ ሳይሆን በዕውቀት እንድትገባበት በማለት የሙዚቃ ትምህርት ቤት እንዲገባ አደረገው። ግርማ ተፈራ ከድምጹ ባሻገር ዛሬም ድረስ የሚጠቀምበትን የህይወት ዘመን የሙዚቃ ዕውቀት የሸመተው የዚህን ጊዜ ነበር። የሙዚቃን ዕውቀተ ስጋ "ተታሎ አይሰጥ ስጋ" እያለ መቅኔውን ከአጥንቱ እየሰረሰረ ሲበላ ከርሞ በአራተኛው ዓመት የሙዚቃ ቆቡን ደፋ።

ከዚህ በኋላ ወደሚወደው ሙዚቃ በኩራት ሲመጣ የመጀመሪያ ሥራው ስለ አባት ያዜመው ዜማ እንደሆነ ይናገራል። በጣም ስለተወደደለት ትላልቅ ሆቴሎች ሳይቀሩ እየሄደ እንዲዘፍንላቸው በጥሪ ቢያጨናንቁትም ምኞቱን የነሳው ጉዳይ እየገጠመው ተቸገረ። ጥሪው ደርሶት ማይኩን ጨብጦ በቆመ ቁጥር ሊዝናና ከመጣው መሃል አባቱን እያስታወሰ ሆድ የሚብሰውን ሰው በተደጋጋሚ መመልከቱ ሥራው ቢቀርስ አስባለውና ተወት አደረገው። እስከዛሬ ስለሠራቸው በርካታ የአልበምና የነጠላ ዜማ ሥራዎቹን ሳነሳ ስለ ድምጽና የአዚያዚያም ብቃቱ እያወራሁ ለቀባሪ አላረዳም። ቀልብን ከስሜት ጠፍረው ሽምጥ የሚያስጋልቡት ሙዚቃዎቹ ይናገራሉ። እንደ ሙዚቃ ግን፤ ግርማ የየትኛው ዘርፍ ተጫዋች ነው ብለን ካልን የአንድ ዓይነት ብቻ አለመሆኑ ነው። ከሥራዎቹ አኳያ ምድብ ከሰጠነው በአመዛኙ የሶል እና ሮክ ዓይነት ስልቶች ናቸው።

የአባቱ ልጅ የሆነው ግርማ ተፈራ አንድ የሙዚቃ ጎተራ ያለው ይመስላል።የራሱን አልበም ይዞ በመጣ ቁጥር ሁሉ ከዚህ ጎተራ ውስጥ እየዘገነ አንድና ሁለት ሙዚቃ የአባቱን ጨመር ያደርግበታል። "ሥራ ፈቶ ሲያይሽ ያንቺ ተመልካች፤ በውበት ቁንጅና ማን ነበር እንዳንቺ" በዚህ ሥራ ውስጥ ከእርሱ አልፎ ያለውን የአባቱን የተፈራ ካሳን ልክ አሳይቶበታል።ተፈራ ካሳ ያኔ ገና በክቡር ዘበኛ ባንድ ውስጥ ሳለ በማርሽ ባንዱ ታጅቦ የሠራው የዚህ ግሩም ዜማ ጥፍጥናው የሚጀመረው ገና ከሙዚቃው መግቢያ ላይ ነው። ከጅምሩ ነብስ ያስኮበልላል። በድጋሚ ግርማ ሲጫወተው ደግሞ ሙዚቃው የነበረው ውበትና ግርማ ኮለል እያለ ወጥቶ ኩልል ብሎ ታየ።"መቼ ትመጪያለሽ" የሚለውንም የቀድሞውን ደምግባቱን ሳይገፍ ከነባንድ ትዝታው ጋር በቅርቡ አስደምጦናል። ቀድሞ ከነበሩበት አንጻር በተደራጁ የሙዚቃ መሳሪያዎች በማዋሃድ በዘመናዊ መልኩ ከማቅረብ በስተቀር እንዳሻው በመሥራት ኃላፊነቱን አልዘነጋም። ከራሱ ሥራዎች በተጨማሪ በየጊዜው ቆንጠር እያደረገ ድንገት የሚያሰማን እኚህ ዜማዎች ከሙዚቃ ጋር በፍቅር እየጣሉ ፍቅርን የሚያሲዙ ናቸው። እርሱ እንደሆን አያልቅበት ነው፤ ወደፊትም የሚያሰማን ገና ብዙ ይኖረዋል። በዚህም አባቱን ዳግም እያስታወስን ግርማ ተፈራንም እያደነቅን እኛም እንዝናናለን። የአባቱ ልጅ ማለት እንግዲህ ለዚህ ዓይነቱ ልጅ ነው፡፡

"እርሱ ለኔ የተለየ ነው። ለርሱ ያለኝ ፍቅርም እጅግ ልዩ ነው። በህይወት ኖሮና ኖሮኝ ሁሉንም ነገር ባደርግለት ይሄን ፍቅሬን ብገልጥለት ደስ ይለኝ ነበር፡፡" የሚሉ የህይወት ዘመን ዐረፍተ ነገሮች አሉት። ይህ ታዲያ ለአባቱ እንጂ ለማንም አይደለም። የአባቱ መውደድ በልቡ ውስጥ ቃላት የማይቋጥሩት ስንኝ ነው። ደግሞ ስለ አባት አዚሚልና በዚያ የአባቶች ቀን ድምጹ እንደተስረቀረቀ ውሎ ያመሻል።ሁሉም ልጆች ከአባታቸው ጥላ ስር ግርማ ተፈራን አብረው እያስታወሱት ይውላሉ። ከአባት የተሰጠ ምርጡ የአባት ስጦታና ግብሂ ነው። ግርማ መቼስ አባቱን ሲወድ ፍቅሩ ወሰን አልባ ዳርቻው ሞላ ነው።"ኖሮ ላሳየው አልቻልኩምና የእርሱን ጥሩነት የምመልሰው ለልጆቼ ጥሩ አባት በመሆን ነው" ይላል ለጥሩነት ምላሹ ጥሩነት መሆኑን ተገንዝቦ። መውደዱ ገኖ ጣር ለመንካቱ ምናልባትም በልጅነት እናቱን በማጣቱ እንደ እናትም አባትም ሆኖ ያሳደገው ድንቅ አባት በመሆኑም ጭምር ነው። በልጅነት ያጣውን የእናቱን ፍቅር በመካሱ "እንደ እናት" የሚለው ጣፋጭ ሙዚቃ ሲያስደምጠን ግጥምና ዜማ ስላገኘ ብቻ አለመሆኑ አሁን ተገለጠልኝ። ያንን የእናትን ዓይነት ፍቅር ላሳየችው ውድ ባለቤቱ የተዜመ ዜማ ነበር። ግርማ በብዙ ለየት የሚያደርገው



ግርማ ተፈራ

ይህ በፍቅራዊ መዓዛ የተቃኘው ልቡ መዳረሻው ወሰን አልባ መሆኑ ነው።በተገኘበት መድረክ ሁሉ ስማቸውን እየጠራ በፍቅር የሚያወድሳቸው አሊያም የሚያመሰግናቸው ቢያንስ ሁለትና ሦስት ሰዎች አይጠፉም።"የት ሀገር የሚለውን አልበሜ ተሠርቶ ለማየት እንደሚፈልግ ሁል ጊዜ በጉጉት ይናገረኝ ነበር። ነገር ግን፤ ማየት የሚፈልገውን ሳያይ በድንገት በሞት ተነጠቅኩኝ" በማለት በእርሱ ላይ የነበረውን የማዲንጎ አፈወርቅን የተስፋ ምኞት በእንባ ይገልጸዋል። ለሞት ክፉት ጥግ የለውም።እጅግ የሚሳሳለትን ሰው ድንገት በሞት ሲነጠቅ ማዲንጎ ሁለተኛው ነው።በወሊድ ወቅት በተፈጠረ የህክምና ስህተት አብዝቶ የሚወዳት ልጁ አያት አድርጋው በዚያው ቀረች። ልጁን እንዳስታቀፈችው ከሞት ጋር ሄዳለች። መሰበር አይሉትን ስብራት ተሰብሮ ወጌሻም የታጣለት ይኼኔ ነበር።

"ግን የት ሀገር?" የወዲህኛው የቅርብ ሥራው ነው። ከአራት ዓመታት በፊት ያለቀለት የነበረ ሥራ ቢሆንም በኮቪድ ወረርሺኝና ጦርነቶች ሳቢያ የመምጫ ጊዜው ተራዝሞ ከርሟል። 2015ን ግን ለመቅረት አልቻለምና በማለቂያው ደረሰ።"የኖህ መርከብ" የሚለውን ዜማም በመጀመሪያዎቹ ላይ አክሎ መጣ። በሙዚቃ ደረጃ ብቻ 20 ያህል ሙዚቀኞች ተሳትፈውበታል። የሚወደው ወዳጁ ማህሙድ አህመድም አንዲት ሥራ ሰጥቶታል። ጥራቱን ለመጠበቅ ሙያዊ ጉልበትም ፈሶበታል። የአልበሙ መጠሪያ የሆነው ዜማም እንዲህ ነው፤

**"በመልክሽ አይደል ወይ በቁንጅናሽ፤**
**የተረታው ልቤ ከብዶት ዝናሽ**
**ልሽሽ አልኩኝ ሳይሽ ከምቸገር፤**
**ልኑር ርቄ ካንቺ ግን የት ሀገር?"**

በግጥም ቴዲ አፍሮና ይልማ ገ/ አብ ተዋህደውበታል። ዜማውን ደግሞ ቴዲ አፍሮ ሲሠራው በሙዚቃ ቅንብሩ ደግሞ አቤል ጳውሎስ ተጠቦበታል፡፡

የመላው ድምጻዊ የአልበም ሥራዎች ተደራሽነት ግን አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል። ከዚህ ቀደም እንደምናውቀው ግርማ ተፈራ እንኳንስ አልበምና ነጠላ ዜማ ሲለቅ እንኳን ገጠር ከከተማው ሸሙናዬ ነበር። ድምጻውያኑ ከሰዋሰው መልቲሚዲያ ጋር ውል ማሰራቸውን ተከትሎ አዳዲስ የሙዚቃ ሥራዎቻቸውን ልናገኝ የምንችለው ከመልቲሚዲያው የኢንተርኔት ማህደር ላይ በመግዛት ብቻ ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። አሁን እንደ ድሮው በዩቲዩብና መሰል ጓዳዎች ውስጥ ማግኘት የለም። እንግዲህ ይህን ተከትሎ ድምጻውያኑ የተሻለ የልፋት ዋጋ ለማግኘት ቢችሉም እንደ ልብ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ተከትሎ በአድማጩ ዘንድ ቅዝቃዜን መፍጠሩ አልቀረም።እየተቀባበሉ በየማህበራዊ ሚዲያው ለማራገብም የማይመች ሆኗል። በዚህም ምክንያት አልበምና ነጠላ ዜማ ባወጡ ቁጥር የሚዘመርላቸው መዝሙርም ቀርቷል። ከእነዚህም አንዱ ግርማ ተፈራ ነው። በቅርቡ በሠራው አልበም እንደቀድሞው ሆ! አልተባለለትም ለማለት ይቻላል። እጅግ ቆንጆ ቆንጆ የሆኑ የድምጽና ምስል ክሊፖችን ጨምሮ ለሽልማት ያበቃውን ምርጥ አልበም ቢሠራም ድምቀቱ ግን ተጓድሏል። ከለምንድነው የበፊት ሥራዎቹ አንጻር ማለት ነው። እንግዲህ በሁኔታው አድማጩ አኩርፎ አሊያም አልገጥምህ ብሎት ይሆናል። ዝምታው ከበዛ ደስታው ጭር ማለቱ አይቀርምና በዋዛ አይታለፍ። ድምጻውያኑም ሆኑ ሰዋሰው መልቲሚዲያ የተሻለውንና የሚበጀውን ሌላ መንገድ ቢያበጁ መልካም ነው።

በስተመጨረሻም የተፈራ ቤተሰብ ዜማቸው እንዲህ ይመስለኛል "አለ ገና፤ ገና አለ ገና..." ምክንያቱም ቀጣዩ የአልበም ሙሸራ የዜመኛው ልጅ የሙዚቀኛው ወንድም መሳይ ተፈራ ነው።በቀጣዩ ሰኔ 1 ቀን አዲሱን አልበሙን ለማስመረቅ በዝግጅት ላይ ነው።"የልቤን" የአልበሙ መጠሪያ ነው። የልቡን ምንስ ሊነግረን ይሆን...ደርሰን የልቡን እንድናደምጥ ሳያጓድል የሰኔ ሰው ይበለን።

# ባህልና ቱሪዝም

## ከመስህብ ልማት ወደ መዳረሻ ልማት ያደገው የክልሉ የቱሪዝም ዘርፍ

**ዳግም ከበደ**



ኢትዮጵያ የብዝሃ ባህል፣ ታሪክና እና ሌሎችም መስህቦች ባለቤት ከሆኑ አገራት ተርታ በቀዳሚነት የምትሰለፍ ነች። ሺህ ዓመታትን ያስቆጠረ አገረ መንግስት፣ በአርኪዮሎጂ ጥናት ምድረ ቀደምት የሚል ስያሜን ያሰጣት የሰው ዘር መገኛ ነች። በተፈጥሮ የታደለች፣ የብዝሀ ህይወት መገኛና የልዩ ልዩ መልከዓ ምድሮች ስብጥርንም በጉያዋ ይዛለች። በሃይማኖት፣ በባህላዊ ምግብና መጠጥ፣ በአልባሳትና ውዝዋዜ ታድላለች። የእነዚህ ሁሉ ጸጋዎች ባለሀብት የሆነችው ይህች ሀገር እነዚህን ሀብቶች ለውጭ ሀገር ጎብኚዎች ማጋራት የሚያስችል አቅምም አላት፤ እንግዳ ተቀባይነቷን ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

እነዚህ ሁሉ ሃብቶች አንድ ስፍራ ወይም አካባቢ ላይ የሚገኙ አይደሉም። ይልቁኑም በሁሉም አቅጣጫና ክፍሎች የምናገኛቸው መስህቦች ናቸው። አክሱም፣ ላሊበላ፣ ሶፍኡመር፣ የጢያ ትክል ድንጋዮች፣ የሃረር ጀጎል ግንብ ጎንደር ፋሲለደስ፣ የባሌ፣ ስሜን እና ሌሎችም የተፈጥሮ ብሄራዊ ፓርኮች እንዲሁም ባህላዊ እሴቶች (የሸዋልኢድ፣ የፊቼ ጫምባላላ፣ የጊፋታ ሌሎችም ሀይማኖታዊ ትርጉም ያላቸው ትውፊታዊ የባህል እሴቶች) በመላው ኢትዮጵያ ብንጓዝ ህያው ሆነው የምናገኛቸው የመስህብ ሀብቶች ናቸው።

ይሁን እንጂ የታደልነውን ሀብት ያህል ወደ ቱሪዝም ኢኮኖሚ ምንጭነት የቀየርነው ሲሶውን አይሆንም። ያለንን የመስህብ ብዛት ያክል ወደ መዳረሻነት የቀየርነውና የቱሪስት መዳረሻ ያደረግነው እጅግ ጥቂት የሚባሉትን ነው።

በኢትዮጵያ በተፈጥሮ፣ ባህል፣ ታሪክና መሰል የቱሪዝም ሀብት ከታደሉ ስፍራዎች ውስጥ የሲዳማ ክልል አንዱ ነው። እነዚህን መስህቦች በማልማት፣ በማስተዋወቅና የቱሪስት መዳረሻ በማድረግ ረገድ ግን አሁንም የሚቀሩ በርካታ ስራዎች እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዛሬ የዝግጅት ክፍላችን በዚህ ላይ ትኩረቱን በማድረግ ‹‹በክልሉ የሚገኙ መስህቦችን ወደ መዳረሻነት ለመቀየርና ማህበረሰቡንና አገርን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ለማድረግ ምን እየተሰራ ነው›› ስንል የሲዳማ ክልል የባህል፣ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ምክትል ሃላፊና የቱሪዝም ዘርፍ ሃላፊ አበበ ማሬሞ ጋር አጭር ቆይታ አድርገናል።

እሳቸው እንደሚሉት የሲዳማ ክልል የባህል፣ የተፈጥሮ፣ የታሪክና ልዩ ልዩ መስህቦችን የያዘ ነው። ይሁን እንጂ ሀብቱ በራሱ በቂ የቱሪዝም ገበያ የሚፈጥር አለመሆኑን ይገልፃሉ። ሀብቶቹም ወደ ቱሪስት መዳረሻነት ተቀይረውና የልማት ስራዎች ተከናውነው ጎብኚዎችን ማስተናገድ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ እንደሚገባ ይገልፃሉ።

‹‹ቱሪስቶች የተለያየ ፍላጎት ነው ያላቸው›› የሚሉት አቶ አበበ፤ የአገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎች እንዲሁም እያንዳንዱም በተናጠል ፍላጎታቸው እንደሚለያይ ይናገራሉ። በዚህ ምክንያት የመዳረሻ ልማቶቹ ሲከናወኑ እነዚህን መሰረት ያደረጉና በጥናት ላይ የተመሰረቱ መሆን እንደሚገባቸው ይገልፃሉ። እንደ አገርም ኢንዱስትሪው ላይ የሚታየው ክፍተት ይህንን በተግባር መሬት ላይ ማውረድ ላይ እንደሆነም ይገልፃሉ። በተለይ ብዝሀ ፍላጎት ያላቸውን ጎብኚዎች እንደየ ፍላጎታቸው ማስተናገድና ከዚያ ከሚገኘው ሀብት ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል አደረጃጀት እስካሁን እንዳልተፈጠረ ይገልፃሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ እምቅ መስህብ ቢኖርም ሁሉም የበሰለና ለቱሪዝም ገበያ መቅረብ እንዲችል የተደረገ አለመሆኑን ያነሳሉ።

መንግሥት በአገር አቀፍ ደረጃ እንደ ጎርጎራ፣ ወንጪ፣ ኮይሻ (ሃላላ ኬላ) እና ሌሎችም የመዳረሻ ልማት ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መስራቱንና እየሰራ አንደሆነም ጠቅሰው፣ የሲዳማ ክልልም ከላይ የተነሳውን የቱሪዝም ገበያ ክፍተት ለመሙላት በማሰብ በመዳረሻ ልማት ላይ ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ እንደሆነ የቱሪዝም ዘርፍ ሃላፊው ይገልፃሉ። የክልሉ መንግሥትም በእነዚህ የልማት ስራዎች ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ መሆኑንም ያስረዳሉ።

‹‹ሲዳማ ክልል ሆኖ ከተደራጀ ወዲህ አዳዲስ መዳረሻዎችን በማበልፀግ ላይ ነው›› የሚሉት አቶ አበበ፤ ቀደም ሲል በይርጋለም፣ ወንዶ ገነትና ሀዋሳ ላይ የተወሰነውን የቱሪዝም እንቅስቃሴና የመስህብ ስፍራዎችን ወደ መዳረሻነት የመቀየር ስራ አሁን ወደሌሎችም ቦታዎችም የማስፋፋት ተግባሩ መጠናከሩን ይጠቅሳሉ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከዘርፉ ያለው ተጠቃሚነት ከ30 በመቶ እንደማይበልጥ ገልፀው፣ አሁን ላይ የቱሪዝም ሀብቶችን በማልማት የቱሪስቱን ቆይታ አራዝሞ የሚያወጣውን ወጪ ከፍ ለማድረግ፣ የቱሪስቱን እርካታ ለመጨመር በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራ መሆኑን ያስረዳሉ።

የመዳረሻ ልማት በባህሪው ጊዜ የሚወስድ ነው የሚሉት የቱሪዝም ዘርፍ ሃላፊው፣ ባሳለፍነው ዓመት ጋራምባ የማህበረሰብ አቀፍ የቱሪስት መዳረሻ ማልማት ውስጥ መገባቱን ይጠቅሳሉ። የመዳረሻ ልማቱ ሶስት ወረዳዎችን የሚያቅፍና ጋራምባ የሚባለውን ተራራ መሰረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ የማልማቱ ስራዎችም በታቀደው መሰረት እየሄዱ መሆናቸውን ተናግረዋል። አሁን ሁለተኛው ክፍል /phase/ ላይ መድረሱንም ገልፀው፣ ከሚተገበሩት ፕሮጀክቶች ውስጥም ኢኮ ቱሪዝም ሎጅ አንዱ መሆኑን አስታውቀዋል። ተራራውን መሰረት አድርጎ ለሚካሄድ ጉብኝትም የመወጣጫ ደረጃዎች ግንባታ አንደሚካሄድ ጠቅሰው፣ ጎብኚዎች ድንን የሚተክሉባቸው ስፍራዎች /camping site/ በፕሮጀክቶቹ ከሚገነቡት መካከል ጥቀቶቹ እንደሆኑ ይናገራሉ።

በመዳረሻ ልማት በተገነባበት ቦታ ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ማህበረሰብ ለቱሪስቶች አገልግሎት በመስጠት ገቢ ማግኘት እንዲችል የማደራጀት ስራ እንደሚሰራ የተናገሩት የቱሪዝም ዘርፍ የቢሮ ሀላፊው፤ ለዚህም ከማህበረሰቡ የተውጣጡ ሰዎችን የማሰልጠን እንዲሁም በቁሳቁስና መሰል መሰረታዊ አገልግሎት መስጫዎችን በማሟላት ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ይገልፃሉ። ይህ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ በቱሪዝም ገበያ ልማቱ ላይ ለክልሉም ሆነ ለአገር ትልቅ አስተዋፆ እንደሚኖረው አመልክተዋል።

የቱሪስት መዳረሻ ማለት መስህብ ያለበት፣ ማህበረሰቡን ያቀፈና ለቱሪስቶች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተሟላ ሁኔታ የሚገኙበት እንደሆነ ያብራሩት አቶ አበበ ፣ ከዚህ ቀደም መስህብ ልማት ላይ ብቻ ትኩረት ይደረግ እንደነበር ይናገራሉ። ይህ ብቻውን በገበያ ልማቱ ላይ ውጤት አለማምጣቱንና መዳረሻ ልማት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ማስፈለጉን ይገልፃሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደር ስር ከሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶች አንዱ ሎከ አባያ ብሄራዊ ፓርክ ነው። ይህንን ፓርክ ወደ መዳረሻነት ለመቀየር እና ማህበረሰቡንም የዚያው አካል ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል። በልማቱም 29 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ብር በመመደብ በፓርኩ ውስጥ ለጎብኚዎች አገልግሎት የሚሰጥ ሳፋሪ ሎጅ አባያ ሀይቅ ዳርቻ ጎን እየተገነባ ይገኛል። ይህንን የመዳረሻ ልማት ተከትሎ የግል ባለሃብቶችም በፓርኩ መሰል አገልግሎት የሚሰጡ ልማቶች ላይ እንደሚሰማሩ ይጠበቃል።

‹‹የቱሪዝም የገበያ ድርሻው የተዳከመበት ምክንያት በመስህብ ስፍራዎቹ አካባቢ ለቱሪስቶች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አሊያም የለማ መዳረሻ ባለመኖሩ ነው›› የሚሉት የቱሪዝም ዘርፍ የቢሮ ሀላፊው፤ ይህንን ችግር በጥናት ላይ ተመስርቶ ለመፍታት ባለሃብቱም ደፍሮ እንዲገባ ለማስቻል የክልሉ መንግሥት ምሳሌ በሚሆኑ የልማት ስራዎች ላይ እየተሳተፈ እንደሆነ ይገልፃሉ። በሀዋሳና አካባቢው፣ በወንዶ ገነት፣ ይርጋለም እና መሰል ቀደም ሲል የሚታወቁ የቱሪስት መዳረሻዎች ላይም እንዲሁ እሴት የመጨመር ተግባር እንደሚሰራም ያስረዳሉ።

በ2016 በጀት አመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ወደ ክልሉ ሶስት ሚሊዮን ቱሪስቶች እንደገቡ የሚናገሩት አቶ አበበ፤ ከእነዚህ ወስጥ 25 ሺህ የሚደርሱት የውጪ ዜጎች መሆናቸውንም አስታውቀዋል። ቀሪዎቹ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች መሆናቸውን ተናግረው፣ በቱሪዝም ዘርፍ አጠቃላይ እንቅስቃሴም አንድ ነጥብ ስድስት በሊዮን ብር ከዘርፉ ገቢ መገኘቱን ይገልፃሉ። ገቢ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ገቢ ጋር ሲነፃፀርም 20 በመቶ የሚሆን ጭማሪ ማሳየቱን ያስረዳሉ። የቱሪዝም ምርትና አገልግሎትን በጥራትና በብዛት ለቱሪስቱ ማዳረስ ከተቻለ ማህበረሰቡንም ሆነ አገርን የሚጠቅም የኢኮኖሚ አቅም መገንባት እንደሚቻልም አቶ አበበ አስታውቀዋል።

አቶ አበበ የቱሪዝም ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ባለሙያዎችን ጥራት ለማሻሻል ቢሮው ከትምህርት ተቋማት ጋር እየሰራ መሆኑን ይናገራሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ትብብርም ጥራት ያላቸው የሆስፒታሊቲና ቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎችን ለማፍራት እንደሚያግዝ ያመለክታሉ። የሀዋሳ፣ ጎንደር፣ አርባ ምንጭ እንዲሁም የቱሪዝም ትምህርትን የሚሰጡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋርም አንዲሁ ባለሙያዎችን እያበቁ እንደሚገኙ ተናግረው፣ እነዚህ ባለሙያዎች በክልሉ መዳረሻዎች ላይ እንደሚሰማሩ ይናገራሉ። ይህም በዘርፉ ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት የቱሪስቱን እርካታ ለመጨመር መልካም ጅምር መሆኑንም አስታውቀዋል።

አቶ አበበ እንደገለጹት፤ በሲዳማ ክልል በቱሪዝም ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ ለመሳብ በዲያስፖራ ኤጀንሲ በኩል በርካታ ስራዎች ይሰራሉ። በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት በየአገሩ ያሉ ዲፕሎማቶችና ቆንፅላ ፅህፈት ቤቶች በኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ አልሚዎችን ይጋብዛሉ፤ የሲዳማ ክልልም የዚህ አካል ነው። የክልሉ መንግሥትም እነዚህን አደረጃጀቶች በመጠቀም በክልሉ የተዘጋጁ የኢንቨስትመንት ቦታዎችን፣ የመስህብ ስፍራዎችንና በዘርፉ ስለተመቻቸው እድል የሚገልፁ ማብራሪያዎችን በመስጠጥ የማስተዋወቅ ተግባር እያከናወነ ይገኛል።

የአገር ውስጥ አልሚዎችም በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ላይ ፍላጎት እያሳዩና እየተሳተፉ ነው የሚሉት የቱሪዝም ዘርፍ ሀላፊው፣ ለአብነትም የስምጥ ሸለቆው ግዙፍ ሀይቅ በሆነው ሎከ አባያ አካባቢ በፓርከ ውስጥ በአባያ ሃይቅ ዳርቻ ለኢንቨስትመንት የሚሆን የሚለማ ቦታ በመሬት ባንክ መዘጋጀቱን ይናገራሉ። ይህ ስፍራ በርካታ ባለሀብቶችን ማስተናገድ እንደሚችል ገልፀው፣ ሰፊ ሃይቅ፣ ፍል ውሃ እና ሌሎች መስህቦችም እንዳሉትና ለአልሚዎች ምቹ መሆኑንም አመልክተዋል። የክልሉ መንግሥትም የባለሃብቶች ፍላጎት ከሆነ እና ለማልማት ዝግጁ ከሆኑ ይህንን ቦታ ለመስጠት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ተናግረዋል። በሀዋሳ፣ በወንዶ ገነትና በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች በሚገኙ መስህቦች ላይ የኢንቨስትመንት ቦታዎች መዘጋጀታቸውንም ጠቁመዋል።

ሲዳማ ክልልን ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከጎበኙት ሶስት ሚሊዮን ቱሪስቶች ውስጥ 25 ሺህ ብቻ የሚሆኑት የውጪ ዜጎች ናቸው ሲሉ ጠቅሰው፣ በንፅፅር ቁጥሩ አነስተኛ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል ብለዋል። የቱሪስት ፍሰቱ አነስተኛ የሆነው መዳረሻዎችን በበቂ ሁኔታ ካለማስተዋወቅ ጋር ብቻ የተያያዘ እንዳልሆነም ተናግረው፣ የቱሪስት ጉብኝት መርሀ ግብር የሚያሰናዱትና የሚሸጡት ዓለም አቀፍ ቱር ኦፕሬተሮች በሚሰጡት የተሳሳተ ምክረ ሀሳብና አገራት በየጊዜው በሚሰጡት የጉዞ ማስጠንቀቂያ ምክንያት እንደሆነም አመልክተዋል።

በተጨማሪ በኢትዮጵያ ሲዳማን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን የማስተዋወቅና ቱሪስቱን የመሳብ ጉዳይ አሁንም በቂ አለመሆኑን አቶ አበበ አስገንዝበዋል። ይህንን ተከትሎ የክልሉም ሆኑ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ባለድርሻዎች በየዓመቱ በሚካሄዱ የሆቴልና ቱሪዝም ፌስቲቫሎች ላይ የዘርፉን መስህቦችና አገልግሎቶች እያስተዋወቁ መሆናቸውን ተናግረዋል። ሌሎች ዲፕሎማሲያዊ መድረኮችን እና ስትራቴጂዎችን በመቅረፅም መዳረሻዎቹን የማስተዋወቁ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል። ክልሉ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር እጅ እና ጓንት በመሆን እንደሚሰራም አስታውቀዋል።

# የልብ ሕሙማን ሕፃናት በማዕከሉ ሕክምና ለማግኘት በአማካይ ከሦስት ዓመት በላይ ወረፋ ይጠብቃሉ

**ማህሌት ብዙነህ**




አዲስ አበባ፡- የልብ ሕሙማን ሕፃናት የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል ሕክምና ለማግኘት በአማካይ ከሦስት እስከ አራት ዓመታት ወረፋ እንደሚጠብቁ በኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል ገለጸ፡፡

በኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ህሩይ አሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕክምና ወረፋ በመጠበቅ የሚገኙ ሕሙማንም አማካኝ የወረፋ መጠበቂያ ከሦስት ዓመት ተኩል እስከ አራት ዓመት የሚፈጅ ነው፡፡ በወረፋቸው አገልግሎት ለማግኘት ሲጠባበቁ ሕይወታቸው የሚያልፍ አሉ፡፡

በሀገሪቱ የልብ ሕሙማን ቁጥር እየጨመረ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም ከ7 ሺህ በላይ የሚሆኑ የልብ ሕሙማን ሕፃናት ወረፋ በመጠበቅ ላይ ናቸው ያሉት አቶ ህሩይ

የሕክምና ወረፋ በመጠበቅ የሚገኙ ሕሙማንም አማካኝ የወረፋ መጠበቂያ ከሦስት ዓመት ተኩል እስከ አራት ዓመት የሚፈጅ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ማእከሉ ላለፉት ረዥም ዓመታት በብቸኝነት ነጻ የሕፃናት የልብ ሕክምና አገልግሎትን እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በዓመት እስከ 450 የሚሆን የልብ ቀዶጥገና እንዲሁም ከ13 ሺህ በላይ ታካሚዎችን የቅድመ እና ድህረ ቀዶ ጥገና ክትትል እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በዓመት ከ780 እስከ አንድ ሺህ የሚሆኑ አዲስ የልብ ሕመም ታካሚዎች መኖራቸውን አመልክተው፤ ይህም በፊት ከነበረው በንጽጽር ሲታይ የታማሚ ቁጥር እየጨመረ ነው ብለዋል፡፡

የልብ ሕክምና አገልግሎት ለማሟላት እየተሠራ ቢሆንም የታካሚዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መሆኑን ጠቁመው፤ በአሁኑ ጊዜም ከችግሩ ስፋት አንጻር አገልግሎቱ በቂ አለመሆኑን አስረድተዋል።

በተለይም በ80 በመቶ በላይ የሚሆኑ አላቂ የሕክምና እቃዎች ከውጭ የሚመጡ በመሆናቸው የዋጋ ንረት ብሎም ችግሩን በአንድ ሆስፒታል መፍታት የማይቻል መሆኑን ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት ማዕከሉ ሁለት የቀዶ ጥገና እና ሁለት ልብ ሳይከፈት የጨረር ሕክምና መስጫን ጨምሮ የተሟላ መሳሪያና የቴክኖሎጂ አቅም እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡ በማዕከሉ 15 በላይ ሐኪሞችና 60 በላይ ነርሶች ያሉት ሲሆን፤ ባለሙያዎቹን ብቁ ለማድረግ ስልጠናና ትምህርቶች እንደሚሰጡ አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ህሩይ ገለጻ፤ ማዕከሉ ሕክምናውን ሀገር ውስጥ መስጠት ከመጀመሩ በፊት ከሁለት ሺ 600 በላይ ሕፃናት ወደ ውጭ ሀገር ሕክምና ተልከዋል። ሕክምናው በሀገር ውስጥ በተሰጠበት 16 ዓመት ውስጥ እስካሁን ከስድስት ሺ በላይ ሕፃናት ነፃ የልብ ሕክምና አግኝተዋል፡፡

በቀጣይ የሕክምና አገልግሎቱን ተደራሽነትን በማስፋት ከየክልሉ ለሚመጡት ቅድመ እና ድህረ ክትትል በአካባቢያቸው እንዲያደርጉ የሚሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የተሟላ ሕክምና አገልግሎት በመስጠት ሁሉም ዜጋ የልብ ሕሙማን ሕፃናትን ለማትረፍ መረባረብ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ የአገልግሎት ወጪዎችን ለመሸፈን ከደጋፊ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚደረጉ ድጋፎችን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ዓለም አቀፍ

## ፕሬዚዳንት ባይደን ይፋ ያደረጉት አዲሱ የጋዛ የተኩስ አቁም እቅድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፕሬዚዳንት ባይደን ይፋ ያደረጉት አዲሱ "የጋዛ የተኩስ አቁም እቅድ" በውስጡ በሶስት ምዕራፎች ይዟል። "ጦርነቱ ማብቂያ ጊዜ ደርሷል" ያሉት ፕሬዚዳንት ባይደን አዲስ ያቀረቡት እቅድ በጋዛ ተኩስ ለማስቆም እና የእስራኤል ታጋቾችን ለማስመለስ የሚያስችል ነው ብለዋል።

በመጀመሪያው ምእራፍ ላይ "ለ6 ሳምንታት የሚቆይ የተኩስ አቁም ይደረጋል" ያሉት ፕሬዚዳንት ባይደን፤ "በዚህ ምእራፍ የእስራኤል ጦር ሰው ከሚበዛባቸው የጋዛ አካባቢዎች ለቀው እንዲወጡ ይደረጋል ሲሉ ተደምጠዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ዕቅድ መሰረት፤ አዛውንቶች እና ሴቶችን ጨምሮ የተወሰኑ የእስራኤል ታጋቾች ይለቀቃሉ፤ በምትኩም በእስራኤል በእስር ላይ የሚገኙ ፍልስጤማውያን ይለቀቃሉ፤ ፍልስጤማውያን ወደ መኖሪያቸው እንዲመለሱ ይደረጋል፤ በየዕለቱ 600 የጭነት መኪናዎች ለጋዛ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያቀርቡ ይደረጋል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሲሆን፤ በዚህኛው ምእራፍ እስራኤል እና ሃማስ ጦርነቱን በዘላቂነት ማቆም በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ይደራደራሉ ያሉት ፕሬዚዳንት ባይደን፤ ንግግሩ እስከቀጠለ ድረስ የተኩስ አቁምም ይራዘማል ብለዋል።

በሶስተኛው ምእራፍ ደግሞ ለጋዛ ትልቅ የመልሶ ግንባታ እቅድ ያካትታል ሲሉም ፕሬዚዳንት ባይደን ተናግረዋል።

ሃማስ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አዲስ የተኩስ አቁም እቅድ ይፋ ማድረጋቸውን ተከትሎ ባወጣው መግለጫ፤ ባይደን ያቀረቡትን የጋዛ የተኩስ አቁም እቅድ በበጎ እንደሚመለከተው አስታውቋል።

ሃማስ በመግለጫው "በዘላቂ የተኩስ አቁም፣ የእስራኤል ጦር ማስወጣት፣ ተፈናቃዮችን ማስመለስ፣ እስረኞችን በማስለቀቅ እና በጋዛ መልሶ ግንባታ ዙሪያ በሚቀርብ ማንኛውም እቅድ ላይ ገንቢ እና አዎንታዊ በሆነ መንገድ ለመወያየት ዝግጁ ነኝ" ብሏል።

የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ በበኩሉ ባወጣው መግለጫ፤ ስምምነቶችን የሚያቀርብ የተደራዳሪዎች ቡድን ማዋቀሩን የገለጸ ሲሆን፤ ነገር ግን ሁሉንም ታጋቾችን ማስመለስ እንዲሁም የሃማስን ጦር እና መንግሥት ማውደምን ጨምሮ ጦርነቱ ግቡን ሳይመታ እንደማይቆም አስታውቋል።

የእስራኤል ሃማስ ጦርነት በፈረንጆቹ ጥምቅት 7 የሃማስ ድንገተኛ ጥቃት ተከትሎ የጀመረ ሲሆን፤ አሁን ስምንተኛ ወሩን አስቆጥሯል። ሃማስ በወቅቱ በድንገት በእስራኤል ላይ በከፈተው ጥቃት አንድ ሺህ 200 ሰዎች ሲሞቱ፤ 250 እስራኤላውን ደግሞ በሃማስ መታገታቸውን እስራኤል በወቅቱ አስታውቃለች።

የሃማስን ጥቃት ተከትሎ እስራኤል በጋዛ እየፈጸመች ባለው የአጸፋ እርምጃ በርካቶች ለህልፈት ተዳርገዋል። የተለያዩ መሰረተ ልማቶችም ወድመዋል።

## የ1 ዓመት ከ5 ወሩ ጋናዊ ሕፃን በዓለም በእድሜ ትንሹ ሰአሊ ተባለ

ሊያም አንክራህ የተባለው ታዳጊ በጋና ዋና ከተማ አክራ ነዋሪ ነው፡፡ ወላጅ እናቱ ቻንትሌ ኩኩዋ ኤግሃን ሰአሊ እና "አርትስ ኤንድ ኮክቴል" የተባለ የስዕል ስቱድዮ ባለቤት ነች፡፡

ልጇ ሊያም የስዕል ተሰጥኦ እንዳለው የተረዳችበትን ሁኔታ ስታስረዳ፤ ገና የ6 ወር ጨቅላ እያለ የስዕል ስራዎቿ ላይ ለማተኮር በሚል ጨርቅ ዘርግታ በቀለም እንዲጫወት ሰጠችው፤ ከዛም በእጆቹ መዳፎች የፈጠራቸው መስመሮች የተጠቀማቸው የቀለም ውህደቶች የስዕል ችሎታ ሊኖረው እንደሚችል እንድታስብ እንዳደረጋት ትናገራለች፡፡

ይህን የመጀመሪያ የሊያም ስዕል "ክሮውል" ወይም "መዳህ" የሚል ስያሜ ወጥቶለት በስዕል ስቱድዮዋ ውስጥ ይገኛል ብላለች::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሊያም ቀለም እና የስዕል ጨርቅ አልተለያዩም የምትለው እናቱ ኤግሀን አንዳንድ ጊዜ እንደ ልጅ ምንም ትኩረቱን ሳይሰርቀው ለሰአታት ያለድካም ቁጭ ብሎ ስዕሎችን እንደሚስል ነው የገለጸችው፡፡

ኤግሀን ልጇ በዓለም ድንቃድንቅ መዝገብ ላይ ስሙ እንዲሰፍር በባለፈው አመት ሰኔ ላይ ነበር ማመልከቻ ያስገባችው፡፡ በተያዘው አመት ህዳር ወር ላይ ከድርጅቱ ባገኘችው ምላሽ ሊያም የሪከርዱ ባለቤት ይሆን ዘንድ የስዕል ኤግዝቢሽን ማዘጋጀት እና መሸጥ እንዳለበት ትረዳለች፡፡

ከዚህ በኋላ ሊያም ለኤግዚቢሽን የሚሆኑ ስዕሎችን እንዲያዘጋጅ ስትረዳው የነበረችው እናቱ በመጨረሻም



ታዳጊው ሊያም በቅርቡ 10 ስእሎችን ለእይታ አብቅቶ ዘጠኙን መሸጥ ችሏል፡፡

ይህን ተከትሎም የዓለም የድንቃ ድንቅ መዝገብ የአንድ አመት ከአምስት ወሩን ሕፃን በእድሜ ትንሹ ወንድ ሰአሊ ሲል ስሙን መዝግቦታል፡፡

ከዚህ ቀደም በእድሜ ትንሽ የሰአሊነት ሪከርድን ይዛ የቆየችው የ11 ወሯ ህንዳዊት አሩሺ ባታንጋር ስትሆን የመጀመሪያ ስዕሏን በ60 ዶላር በመሸጥ ሪከርዱን ይዛ ትገኛለች። ጋናዊው ሊያም ደግሞ በእድሜ ትንሹ ወንድ ሰአሊ በመባል ሪከርዱን ተጋርቷታል።




# ልጆች በሥራ ፈጠራ

**እየሩስ ተስፋዬ**

እንዴት ናችሁ ልጆች? ሠላም ናችሁ? ትምህርት እንዴት ነው? ባጠናቀቅነው ሳምንት ሁሉም የስድስተኛ እና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ሞዴል ፈተና እንደወሰዱ ይታወቃል አይደል ልጆች። የተፈተናችሁ ልጆች ፈተና እንዴት ነበር? ለፈተና በሚገባ ተዘጋጅታችሁ ነበር? በጣም ጎበዞች። በቻላችሁት መጠን እንዳጠናችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ስለዚህም ልጆችዬ ከሞዴል ፈተና ብዙ ተምራችሁ ዋናው ፈተና ሲደርስ በብቃት ፈተናውን ለመውሰድ የተማራችሁትን ትምህርት በመከለስ፤ ለፈተና ራሳችሁን በሚገባ ማዘጋጀት እና ማጥናት ይኖርባችኋል። ሌላው ደግሞ ልጆችዬ ያለምንም መደናገጥ እና ጭንቀት ፈተናችሁን መውሰድ አለባችሁ።

ልጆችዬ፣ በእርግጥ ዛሬ ስለፈተና ልናወራችሁ አይደለም። በሌላ ጊዜ እንዴት መዘጋጀት እንዳለባችሁ፤ እንዲሁም ምን ማድረግ እንደሚኖርባችሁ የሚጠቁም ጽሁፍ ይዘን ለመቅረብ ቃል በመግባት ዛሬ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን ስለሠሩ ተማሪዎች በጥቂቱ የምናስተዋውቃችሁ ይሆናል።

ሳለአምላክ ምስጋናው ይባላል። ጆይንት ሰክሰስ አካዳሚ ትምህርት ቤት ነው የሚማረው። ለፈጠራ ሥራ የተለየ ፍቅር አለው። ፍቅር ብቻ ሳይሆን ችሎታ እንዳለውም በተግባር አሳይቷል። በ9ኛው ከተማ አቀፍ የሳይንስ ፈጠራ ሥራ አውደ ርዕይ ላይ ተሳትፏል። ተማሪው የሠራው ዘመናዊ መጸዳጃ ቤት ሲሆን፤ ይህ መጸዳጃ ቤት ከሌሎች ለየት ያለ እንደሆነ ይናገራል። መፀዳጃ ቤቱ መስማት ለተሳናቸው ወይም መናገር ለማይችሉ ሰዎች በመጸዳጃ ቤት ውስጥ ሰው እንዳለ መብራት በማብራት የሚያመላክት ነው። ለአይነ ሥውራንም ድምጽ በማሰማት ከሌሎች ጋር የሚግባቡበትን የፈጠራ ሥራ ሰርቷል።

ሌላው ከመጸዳጃ ቤት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ሠዎች መጸዳጃ ቤት ከገቡ በኋላ ውሃ አይደፉም። ንጽህናው የተጠበቀ መጸዳጃ ቤት እንዲኖር አንድ ሰው የውሃ መድፊያውን ካልተጫነ በሩ እንዳይከፈት የሚያደርግ የፈጠራ ሥራ ሰርቷል። በዚህ ፈጠራ ሥራ ውሃ መድፋት እንደሚገባ ግንዛቤ ለመስጠት በሚገባ ይጠቅማል ብሎ ያምናል። እርሱ ይህን የፈጠራ ሥራ ለመሥራት ምክንያት የሆነው በብዙ አካባቢዎች ላይ ንጽህናቸውን ያልጠበቁ መጸዳጃ ቤቶች መኖራቸውን በማየቱ ነው። ደግሞም ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ባለመሆናቸው ይህ ነገር ሊታረም ይገባል በሚል መልካም ሃሳብም ተመሥርቶ ነው።

ብሌን አይቼው ሌላኛዋ የፈጠራ ችሎታ ያላት ተማሪ ናት። እርሷ የሠራችው አራት ነገር በአንዴ የሚይዝ ዕቃ ነው። ሳጥን በሚመስል ዕቃ ውስጥ የሻይ ማፍያ፣ ቡና ወይም ውሃ ማፍያ፣ ቡና መፍጫ ስቶቭ ነው። የስራ ፈጠራው በአንድ ቦታ ላይ ቡናው ተቆልቶ፣ ተፈጭቶ እና ተፈልቶ ማጠናቀቅ የሚቻልበት እንደሆነም አስረድታለች። በቀጣይ በፈጠራ ሥራ ላይ በስፋት በመሠማራት፤ እንዲሁም ችግር ፈቺ የሆኑ ምርቶችን የማድረስ ፍላጎት እንዳለት የገለጸችው ተማሪ ብሌን ሌሎች ልጆችም የሚሠሩትን የፈጠራ ሥራ ሌሎች አይተው ሃሳብ እንዲሰጧቸው እንዲያደርጉ ትመክራች።


**ልጆችዬ፣ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት ከሚጥሩ ተማሪዎች ምን ተማራችሁ? ትምህርት ከመማር ጎን ለጎን የፈጠራ ሥራ መሥራት እንደሚቻል እና በቀላል ወጪ የሚሠሩ የፈጠራ ሥራዎችን መከወን እንደሚቻል በሚገባ ተምራችኋል**

ዲናኦል መንግሥቱ በአንዶሪ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምነተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ‹‹ዲናር›› ብሎ የሰየመው በአንድ ጊዜ ሁለት ነገር መሥራት የሚችል ኦቭን (ምግብ ማብሰያ) ነው የሠራው። ጥቅሙ ከኦቭን በላይ ነው ያለው ተማሪው፣ በአንድ ጊዜ ከላይ እንጀራ የሚጋግር፤ ከሥር ደግሞ ድፎ ዳቦ ለመድፋት የሚያስችል ነው። የሠራው የፈጠራ ሥራ በአነስተኛ ዋጋ እና ከወዳደቁ ሽቦዎች የተሠራ እንደሆነም ተናግሯል። በተለይም ጠባብ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች በአንድ ዕቃ ሁለት ነገር መሥራት የሚችል በመሆኑ ለጠባብ ቤት እጅግ ተመራጭ እንደሆነ ይገልጻል። በተጨማሪም በአንድ ኤሌክትሪክ ሃይል ሁለት ነገር በአንድ ጊዜ የሚሠራ ስለሆነ የኤሌክትሪክ ፍጆታን በመቆጠብ በኩልም የሚሠጠው ጥቅም እንዳለው ይናገራል።

የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ዲናኦል ለወደፊት በሶፍት ዌር ኢንጂነሪንግ ተመርቆ አገሩን ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጎት አለው። በተጨማሪም ፍላጎቱን ለማሳካት በርትቶ እየተማረ እንደሆነ ይናገራል። እንደ እርሱ የፈጠራ ሥራ የሚሠሩ ወይም የሚሞክሩ ተማሪዎች የሠሩትን ለመምህራን እና እውቀቱ ላላቸው ሰዎች በማሳየት፣ በሚዘጋጁ አውደ ርዕዮችም ሆነ ውድድሮች ላይ ቢሳተፉ እሱ እንዳገኘው የልምድ ልውውጥ እና አይተው የማያውቁትን የፈጠራ ችሎታዎችን ለማየት እንደሚያግዛቸው ይጠቁማል።

ልጆችዬ፣ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት ከሚጥሩ ተማሪዎች ምን ተማራችሁ? ትምህርት ከመማር ጎን ለጎን የፈጠራ ሥራ መሥራት እንደሚቻል እና በቀላል ወጪ የሚሠሩ የፈጠራ ሥራዎችን መከወን እንደሚቻል በሚገባ ተምራችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ልጆችዬ፣ ለዛሬው በዚሁ ብንሠነባበት መልካም አይመስላችሁም? በጣም ጥሩ። ሳምንት በሠላም ለመገናኘት እንዲያበቃን በመመኘት እስከዛው መልካም የእረፍት እና የትምህርት ሳምንት ይሁንላችሁ እንላለን!!

# ስፖርት



# "በራሪዋ እመቤት"

**ብርሃን ፈይሳ**

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተጠናቀቀ ሶስት ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ በ1948 የእንግሊዟ ለንደን ከተማ ታላቁን ኦሊምፒክ አዘጋጀች። በጦርነቱ ምክንያት የተቀዛቀዘውን ስፖርት ለማነቃቃት ኦሊምፒኩ ምቹ አጋጣሚ ቢሆንም አዲስና ምርጥ ስፖርተኛን ከተቀረው ዓለም የሚያስተዋውቅ መድረክ መሆኑ በይበልጥ አጓጊ አድርጎት ነበር። የስፖርት ቤተሰቡ በእርግጥም የናፈቀውን የአትሌቶች የብቃት ልክ ለመመልከት ቻለ፤ ይሁንና አቀባበሉ ሁለት መልክ ነበረው። የኦሊምፒኩ ወደር የለሽ ተወዳዳሪ 4 የወርቅ ሜዳሊያዎችን መሰብሰብ ተመልካቹን ‹‹አጃኢብ›› ቢያሰኝም፤ የዚህ ብቃት ባለቤት ሴት አትሌት መሆኗ ግን ለብዙዎች ሊዋጥላቸው ያልቻለ ጉዳይ ነበር።

የሴት ስፖርተኞች ተሳትፎ በሚወዳደሩባቸው ስፖርቶች እንዲሁም በቁጥራቸው እግድ ተጥሎበት እያዘገመ በነበረበት በዚያ ዘመን ድንቅ ብቃቷን ያሳየችው ይህቺ ሴት የሁለት ልጆች እናት ነበረች። ነገር ግን አስገራሚው ብቃቷ ‹‹በራሪዋ እመቤት›› የሚል ሙገሳ አሰጥቷታል። ችሎታዋን በግልጽ እየተመለከቱ ነገር ግን መቀበል ያልፈለጉ የጾታ እኩልነት ደፍጣጮች አትሌቷን ቢቃወሙም፤ እሷ ግን የሴቶችን አቅምና የጥንካሬ ልክ ሚዛን ላይ ያወጣች የስፖርቱ ዓለም ጀግና ናት። ኦሊምፒክ በእኩል የስፖርት ዓይነት እኩል ተሳትፎን ለማስተናገድ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ ቢፈጅበትም ይቺን አይነት ብርቱ ግን ታሪክ ሲያወሳት ይኖራል።

የኦሊምፒክ ጀግናዋ አትሌት ፍራንሲኔ ኮይን ትባላለች። የሆላንድ ተወላጅ ናት። አትሌቷ እ.ኤ.አ በ1935 የስፖርቱን ዓለም ብትቀላቀልም የነበራት ተሰጥኦና ችሎታ በቀጣዩ ዓመት በርሊን ላይ በሚካሄደው ኦሊምፒክ ሊያሳትፋት የሚችል ነበር። ነገር ግን ከኦሊምፒኩ መካሄድ አስቀድሞ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በመነሳቱ ህልሟ ሊሳካ አልቻለም። በዚህ መካከልም የስፖርት



ኔዘርላንዳዊቷ አትሌት ፍራንሲኔ ኮይን

ዘጋቢና የአትሌቲክስ አሰልጣኝ ከሆነ ሰው ጋር ትዳር በመመስረት የሁለት ልጆች እናት ለመሆን በቃች። ይህንን ተከትሎም የአትሌቲክስ ህይወቷ አብቅቶ እንደብዙዎቹ ሴቶች በቤት እመቤትነት ተወስና ትቀራለች የሚለው የብዙዎች እምነት ነበር። ወቅቱ ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸው የማይታመን እንደመሆኑ ባለቤቷም ጭምር የዚሁ እምነት አራማጅ ነበር። ከኮይን ጋር ከተዋወቁ በኋላ ግን ይህ አመለካከት ተቀርፎ ይካሄዱ በነበሩ የሃገር ውስጥ እና አህጉር አቀፍ ውድድሮች እንድትሳተፍ ከማድረግ ባለፈ ከወሊድ ጥቂት ሳምንታት በኋላ ወደ ልምምድ ስትመለስ በማገዝ አብሮነቱን ማስመስከር ችሏል።

ለንደን ኦሊምፒክ ላይ ሀገሯን ወክላ ለመሳተፍ ዝግጅት በማድረግ ላይ ሳለችም በርካቶች ‹‹ቤት ሆነሽ ልጆችሽን አሳድጊ›› በማለት ተስፋ ሊያስቆርጧት ሞክረዋል። ከዚያም ባለፈ የ30 ዓመቷ አትሌት ‹‹ውጤታማ ለመሆን እጅግ ያረጀች›› በማለት የመገናኛ ብዙሃን ጭምር ዘመቻ ከፍተውባት ነበር። ብርቱዋ አትሌት ግን ይህንን ለመሰለው ትችት በቀላሉ እጅ የማትሰጥ በመሆኗ ከቡድኑ ጋር የኦሊምፒክ መንደርን ተቀላቀለች። ወደ መም ስትወጣም ከቀንደኛ ተቺዎቿ መካከል አንዱ የሆነውንና ከተመልካቹ መካከል የተቀመጠውን ሰው ‹‹ምን እንደማደርግ አሳይሃለሁ›› በማለት በራስ መተማመኗን አንጸባርቃም ነበር።

በእርግጥም ቃሏን በተግባር አውላ በችሎታዋ ተቺዎቿን ዝም ማሰኘት ችላለች። ኮይን የመጀመሪያ ውድድሯ 100 ሜትር ሲሆን በአሳማኝ ብቃት ግማሽ ፍጻሜ በመድረስ በዝናባማ የአየር ሁኔታ በተደረገው የፍጻሜ ውድድርም አሸናፊ ለመሆን ቻለች። ይህም አትሌቷን የመጀመሪያዋ የኦሊምፒክ ሜዳሊያን ያጠለቀች ኔዘርላንዳዊት አድርጓታል። በዚህ ብቻ ሳታበቃም በ200 ሜትር፣ 80 ሜትር መሰናክል፤ እንዲሁም 4 በ400 ሜትር ሪሌ በድምሩ 4 የወርቅ ሜዳሊያዎችን ማስቆጠር ቻለች። አምስተርዳም ስትገባም ከህዝብ እስከ ቤተመንግስት ብሄራዊ የጀግና አቀባበል ሲደረግላት በርካታ ስጦታዎችም ተዥጎደጎዱላት።

ሞራል የሚነኩ ዘገባዎችን ሲያስተላልፉ የቆዩ የመገናኛ ብዙሃን በበኩላቸው በትችቱ ምትክ ‹‹በራሪዋ እመቤት፣ በራሪዋ ኔዘርላንዳዊት፣ ...›› በሚል ማንቆለጳጰስ ጀመሩ። ታሪካዊቷ ኮይን ከዚያ በኋላ በተደረጉ የኦሊምፒክ መድረኮች ላይ ባትታይም በአህጉር አቀፍ ውድድሮች ላይ ግን በተለመደ ውጤታማነቷ ዘልቃ የአትሌትነት ህይወቷን አብቅታለች። ነገር ግን የኔዘርላንድ አትሌቲክስ ቡድንን በመምራት፤ እንዲሁም አሁንም ድረስ በስሟ የሚጠራ ዓመታዊ ውድድርን በመመስረት የምትወደውን ስፖርት ስታገለግል ቆይታለች።

በርካታ ሽልማቶችና ክብሮች የተበረከቱላት አትሌቷ በዓለም አትሌቲክስ ‹‹የክፍለ ዘመኑ ምርጥ ሴት አትሌት›› በሚልም ሰይሟታል። ኮይን እ.ኤ.አ በ2004 ከዚህ ዓለም ብታርፍም ኔዘርላንዳዊያን የተለያዩ ስፍራዎች ላይ ሃውልት በማቆም፤ እንዲሁም ልምምድ ትሰራባቸው የነበሩ ስፍራዎችንና የአትሌቲክስ ማሰልጠኛዎችን በስሟ በመሰየም ጀግኒታቸውን ያከብራሉ።